www.abyssinialaw.com



9ኛ አመት ቁጥር 37

9th Year No 37

ባህር ዳር ጥቅምት 30 ቀን 1997 ዓ.ም

Bahir Dar November 9, 2004

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

# ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA



| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ<br>ብር 6.30<br>Unit Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የ ፖ.ሣ.ቁ<br>312<br>P.o. Box |



| ማውጫ | Contents |
|---|---|
| **ደንብ ቁጥር 22/1996 ዓ.ም**<br>በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ አባላት መተዳደሪያ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ | **Regulation No.22/2004**<br>The Amhara National Regional State Prison Police Officers' Administration, Council of the Regional Government Regulation. |

## ደንብ ቁጥር 22/1996 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ አባላትን ለማስተዳደር የወጣ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ

## REGULATION NO.22/2004

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE ADMINSTRATION OF PRISON POLICE OFFICERS IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

www.abyssinialaw.com



በየደረጃው የሚገኙትን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ አባላት ቅጥር፣ ምደባ፣ ዝውውር፣ ምልመላ፣ የደረጃ ዕድገትና ስንብት የሚወሰን ክልል አቀፍ የመተዳደሪያ ደንብ አውጥቶ በሥራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ም/ቤት በብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና በክልሉ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ማቋቋሚያ፣ እንደገና ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 67/1994 ዓ/ም አንቀጽ 24 ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአማራ ብሐራዊ" ክልላዊ መንግስት ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ አባላት መተዳደሪያ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ ቁጥር 22/1996 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

ሀ. "ማረሚያ ቤቶች"፣ "የማረሚያ ቤቶች ፖሊስ"፣ "ታራሚ"፣ "ቢሮና የቢሮ ኃላፊ" የተሰኙት ቃላትና ሀረጎች በክልሉ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ማቋቋሚያ፣ እንደገና ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 67/1994 ዓ/ም አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1፣2፣3 እና 4 ድንጋጌዎች ሥር የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

ለ. "አዋጅ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

WHEREAS, it is found necessary to issue and implement a region wide administrative that determines the recruitment, assignment, transfer, selection, upgrading and dismissal of the amhara National Regional State Prison Police Officers at all levels in the region.

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Regional Government in accordance with the powers vested in it under the provisions of art. S8, sub art.7 of the National Regional Constitution and art.24 of the Regional Prison Administration Offices establishment, re-organization and determination of powers and duties proclamation No. 67/2002, hereby issues this regulation as follows

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This regulation may be cited as "The Amhara National Regional State Prison Police Officers Administration, Council of Regional Government Regulation No. 22/2004"

### 2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this regulation:

A. The terms and phrases such as "Prisons" "Prisons Police Officer", "Prisoner", "Bureau and Bureau head" shall take the definitions given to them under art. 2, sub arts. 1, 2, 3 and 4 of the prison administration office establishment, re-organization and determination of powers and duties proclamation No.67/2002.

B. **"Proclamation"** means the Amhara National Regional

www.abyssinialaw.com



ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ማቋቋሚያ፣ እንደገና ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 67/1994 ዓ/ም ነው፡፡

State prison administration office establishment, re-organization and determination of powers and duties proclamation No. 67/2002.

ሐ. **"ጽ/ቤት"** ማለት ከፍ ብሎ በተጠቀሰው አዋጅ የተቋቋመው የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ነው፡፡

C. **"Office"** means the prison administration office established under the proclamation stated herein above.

መ. **"የማዕረግ ዕድገት"** ማለት አንድን የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከያዘው ማዕረግ ቀጥሎ ወዳለው ማዕረግ ማሣደግ ነው፡፡

D. **"Rank promotion"** means promoting a prison police officer from the rank he holds to the next higher rank.

## 3. የደንቡ ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ የጽ/ቤቱን ኃላፊና በክልሉ ሲቪል ሠርቪስ ሕግ መሠረት የሚተዳደሩትን ሲቪል ሠራተኞች ሣይጨምር በማናቸውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 3. Scope of Application of the Regulation

This regulation shall, with the exception of the head of the office and those civil servants administered pursuant to the regional civil service laws, be applicable to any prison police officers.

## ክፍል ሁለት

## ስለምልመላ፣ ስልጠና፣ ቅጥር፣ ምደባና ዝውውር

## PART TWO

## RECRUTIMENT, PLACEMENT AND TRANSFER

## 4. ምልመላና ቅጥር

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች የሚያሟላና ፍላጐት ያለው ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው በማረሚያ ቤት ፖሊሲነት መመልመል ይችላል፡-

ሀ. ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ

ለ. ለፌዴራሉና ለክልሉ ህገ‌ጋት መንግሥታት ታማኝ የሆነ

ሐ. መልካም ሥነ-ምግባር ያለው

መ. ዕድሜው ከ18 ዓመት ያላነሰ

ሠ. ቢያንስ የ10ኛ ክፍል ትምህርቱን ያጠናቀቀ

## 4. Selection and Recruitment

1. Any natural person wishing to serve as a prison police officer may, upon fulfillment of the criteria specified here below, be recruited as such where he:

a. Is an Ethiopian citizen;

b. Loyal to the Federal and Regional Constitutions;

c. Has a good ethical conduct;

d. Is not below the age of 18 years;

e. Has at least completed 10th grade in pursuance of his education;

www.abyssinialaw.com



ረ. ለማረሚያ ቤት ፖሊስነት የሚያበቃ አቋምና የተሟላ ጤንነት ያለው

ሰ. የወንጀል ጥፋተኝነት ሪከርድ የሌለበት

ሸ. ይህንን ደንብ በማይቃረን አኳኋን እንደ ሁኔታው ጽ/ቤቱ የሚያወጣቸውን ሌሎች ተጨማሪ መመዘኛዎች ሲያሟላ

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለማረሚያ ቤት ፖሊስነት የሚደረገው ምልመላ የጾታና በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ሚዛናዊ ተዋጽኦ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለማረሚያ ቤት ፖሊስነት የተመለመለ ማንኛውም ሰው በጽ/ቤቱ የሚዘጋጀውን የቅጥር ውል ይፈርማል፣ ቅጥሩ የሚፀናበት ጊዜም በቅጥር ውሉ ላይ ይገለፃል፡፡

4. የማረሚያ ቤት ፖሊስ ምልመላና የማስታወቂያ ሒደት በመመሪያ ይወሰናል፡፡

5. ማንኛውም በማረሚያ ቤት ፖሊስነት የተቀጠረ ሰው ሰባት ዓመት የአገልግሎት ግዴታ ይኖርበታል፣ የሰባት ዓመቱ የግዴታ አገልግሎት ዘመን መቆጠር የሚጀመረው ስልጠናውን አጠናቆ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

## 5. ስለ ሥልጠና

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት መሠረታዊ የፖሊስ ስልጠና ይሰጠዋል፣

2. የስልጠናው ዓላማ ለህገ-መንግስቱ መከበር የሚቆምና

f. Is physically fit and healthy enough to be recruited as a prison police officer;

g. Has had no criminal conviction record;

h. Fulfils other additional criteria which the office may set out without prejudice to this regulation.

2. Without prejudice to the provisions of sub art.(1) of this article hereof, any selection carried out for a prison police recruitment shall take in to consideration the fair and balanced representation of all sexes as well as nation-nationalities and peoples residing in the Regional State.

3. Any person recruited to be a prison police officer in accordance with sub-art. (1) Of this article hereof, shall sign an employment contract prepared by the office. The effective date of the employment shall be specified in such contract.

4. The Process of selection of prison police officers and notification thereof shall be determined by a directive.

5. Any person recruited to be a prison police officer shall serve for a compulsory period of seven years; provided, however, that such a period of compulsory service shall be bound to commence, having been calculated as of the date of the completion of his training thereto.

## 5. Training

1. Any prison police officer shall receive basic police training before commencing his duties.

2. The objective of the training is to create a professional prison police officer dedicated to and capable of

www.abyssinialaw.com



ብቃት ያለው የማረሚያ ቤት ፖሊስ ባለሙያ መፍጠር ነው፡፡

3. የስልጠናው አይነት በሶስት ይከፈላል እነሱም፡-

ሀ. መሠረታዊ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ስልጠና

ለ. ከማረሚያ ቤት ፖሊስነት ጋር የሚገናኝ የሙያ ስልጠናና

ሐ. ለአመራር የሚያበቁ ስልጠናዎች ናቸው፡፡

4. ስልጠናውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ዝርዝር ሁኔታዎች ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ፡፡

5. ማንኛውም ሰልጣኝ በስልጠና ወቅት፡-

ሀ. በሚመደብበት የስልጠና ኘሮግራም የመሣተፍ፣

ለ. የሚገባበትን ማሠልጠኛ ተቋም ውስጣዊ የአሠራር ደንቦችና መመሪያዎች የማክበር፣

ሐ. የተመደበበትን የስልጠና መስክ ለማቋረጥ፣ ለመቀየር ወይም ለማራዘም ሲፈልግ ጽ/ቤቱን በቅድሚያ የማስፈቀድ ግዴታ አለበት፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ከፊደል ተራ ቁጥር “ሀ” እስከ ፊደል ተራ ቁጥር “ሐ” የተጠቀሱት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በሚገኙበት ወቅት ምግብ፣ የደንብ ልብስ፣ ጫማ፣ ነፃ የመኝታና ህክምና አገልግሎት እንዲሁም ቢሮው በሚወስነው መሠረት የኪስ ገንዘብ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

## 6. ቃለ መሃላ

1. ማንኛውም የክልሉ ማረሚያ ቤት ፖሊስ አባል

enforcing the constitution.

3. The types of the training are categorized in to three. These are:

a. Basic prison police training;

b. Professional training related to prison police service; and

c. Trainings enabling one to assume managerial position.

4. Particular requirements necessary for the execution of the training shall be determined by a directive which the Bureau may issue thereto.

5. Any trainee shall, while in training :

a. Participate in the training program in to which he is assigned;

b. Adhere to the internal regulations and directives of the training institution in to which he is placed;

c. Have the permission of the office prior to terminating, changing or extending the filed of training in which he is assigned to.

6. Without prejudice to the provisions stated under letters ‘a’ up to ‘c’ of sub art. 5 of this article hereof, any new trainee shall, while in training, be entitled to get food, closing, shoes, free lodging and medical services as well as pocket money pursuant to the decision by the bureau.

## 6. Oath

1. Any member of the prison police of the regional state who has completed his basic prison police

www.abyssinialaw.com



መሠረታዊ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ስልጠናውን እንዳጠናቀቀ ስራ ከመጀመሩ በፊት የሚከተለውን ቃለ መሀላ ይፈፅማል፡

እኔ ------------- የክልሉንና የፌዴራሉን ህግጋት - መንግሥታትና ሌሎች ህጐች ላከብርና ላስከብር፣ የታራሚዎችን ሰብአዊ መብት ልጠብቅና ላስጠብቅ፣ የግል ጥቅም ላልፈልግ እና በሌላ በማናቸውም ምክንያት አድሎ ሳላደርግ በሃቀኝነት፣ በቅንነትና በትጋት ኃላፊነቴን ለመወጣት ቃል እገባለሁ፡፡

2. የተፈፀመው ቃለ መሃላ በማረሚያ ቤት ፖሊሱ ተፈርሞ በግል ማህደሩ ውስጥ ይቀመጣል፡፡

training program shall, before commencing his duties, take the following oath:

"I ---------------- solemnly swear that I shall pledge to respect and enforce the Regional and Federal constitutions and other laws, to protect the human rights of prisoners, not to seek personal gains as well as to avoid discrimination for any reason and carry out my responsibilities with loyalty, integrity and diligence."

2. The oath executed shall, after having been duly signed by the prison police officer, be kept in his personal file.

## 7. ምደባ

ማንኛውም ሰልጣኝ ሥልጠናውን ከጨረሰ በኂላ በሰለጠነበት ሙያ ያገለገለ ዘንድ በጽ/ቤቱ ወይም በየደረጃው ባሉ ማረሚያ ቤቶች ይመደባል፡፡

## 7. Assignment

Any trainee shall, upon completion of his training, be assigned in the office or those prisons found at all levels to render service in accordance with the area of his qualification.

## 8. ዝውውርና በተጠባባቂነት ስለመመደብ

1. ጽ/ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውንም የማረሚያ ቤት ፖሊስ በመስሪያ ቤቱ ውስጥ በተመሣሣይ የሥራ ደረጃና ደመወዝ ከአንድ የሥራ መደብ እኩል ደረጃ ወዳለው ሌላ ተመሣሣይ የሥራ መደብ ወይም ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ በማዛወር ሊያሠራ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በውስጥ ዝውውር ሊሞላ በሚችል ክፍት የሥራ መደብ ላይ መስራት የሚፈልጉ ሌሎች የማረሚያ ቤት ፖሊሶች ሲኖሩ ዝውውሩ የሚፈፀመው በውድድር ይሆናል፡፡

## 8. Transfer and Temporary Assignment

1. The office may, wherever it finds it necessary for the duties, transfer and engage any prison police officer from one position to another position of an equal grade and salary or from one place of work to another, with similar work grades and salaries.
2. Any assignment envisaged under sub-art.(1) of this Article hereof shall be carried out on the basis of completion where there are other prison police officers interested to be placed in any position of work open for occupation by an internal transfer.

www.abyssinialaw.com



3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖር ጽ/ቤቱ ሥራው እንዳይበደል የአንድን የማረሚያ ቤት ፖሊስ ደመወዝ ሣይቀንስና ደረጃውን ወይም የያዘውን የሥራ አይነት ሣይጠብቅ ከአንድ አመት ላልበለጠ ጊዜ በጊዜአዊነት አዛውሮ ማሠራት ይችላል፡፡

4. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ በጤና መታወክ ምክንያት በያዘው የሥራ መደብ ላይ ወይም ባለበት የሥራ ቦታ ሊሠራ አለመቻሉ በሃኪም ማስረጃ ሲረጋገጥ፡-

   ሀ. በተመሳሳይ ደረጃ ሊመደብ የሚችልበት ክፍት የሥራ መደብ ካለ በያዘው ደረጃ፣ ወይም

   ለ. በተመሳሳይ ደረጃ ሊመደብ የሚችልበት ክፍት የሥራ ቦታ ከሌለና ፖሊሱ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለመስራት ፈቃደኛ ከሆነ ደረጃው ተቀንሶ ወደ ሚስማማው የሥራ መደብ ወይም የሥራ ቦታ ይዛወራል፡፡

5. ሁኔታዎች ሲያስገድዱ ጽ/ቤቱ አንድን የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከፍ ያለ ደረጃ ባለው የሥራ መደብ ላይ በተጠባባቂነት እንዲሠራ ማድረግ ይችላል፡፡

6. አንድን የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከአንድ አመት በላይ በተጠባባቂነት ማሠራት አይቻልም

7. የአንድ ማረሚያ ቤት ፖሊስ የሥራ መደብ የተሠረዘ እንደሆነ በመስሪያ ቤቱ ውስጥ በተመሣሣይ ደረጃ ወደ አለው የሥራ መደብ መዛወር ይኖርበታል፡፡

8. በተመደበበት የሥራ ቦታ ወይም ክፍል ቢያንስ ሁለት ዓመት ያገለገለ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ለጽ/ቤቱ የዝውውር ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ

3. Notwithstanding the provision of sub-art.(1) of this article, the office may temporarily assign, for the per pose of the duty, a prison police officer to a position of work, without affecting his salary, irrespective of his grade and the type of work he occupies for the period, not exceeding one year.

4. Where it is medically proven that any prison police officer is, because of ill-health, unable to keep on working in the position or place of work he has already occupied thereof, he shall be transferred to another suitable position or place of work:

   a. With the same grade as he has been holding, if there exists a vacant position of work for possible assignments; or

   b. With a lower grade, where a vacant position of the same grade is not available and he is, therefore, willing to be transferred to a position of lower grade consequently.

5. Where circumstances so require, the office may assign a prison police officer to a higher position in an acting capacity.

6. No a prison police officer may be assigned in an acting capacity for more than a year.

7. Where the position of a prison police officer is cancelled, he shall be transferred to another position of equal grade within the office.

8. A prison police officer who has served at least for two years in a work place or department he has been assigned to may apply to the office for transfer. Details of the execution shall be determined by a

www.abyssinialaw.com



ይወሰናል፡፡

directive to be issued by the Bureau.

## ክፍል ሦስት

## ስለደመወዝና ልዩ ልዩ አበሎች

## PART THREE

## SALARY AND VARIOUS ALLOWANCES

### 9. ስለደመወዝ ስኬል

1. ጽ/ቤቱ ለማረሚያ ቤት ፖሊሶች የሚያገለግሉ የደመወዝ ስኬሎችን አጥንቶ በቢሮው አማካኝነት ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ክፍል እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡
2. የደመዝ ስኬሉ ለእያንዳድ የማእረግ ደረጃ መነሻና መድረሻን እንዲሁም በየጊዜው የሚደረገውን የደመወዝ ጭማሪ የሚያመለክቱ እርከኖች ይኖሩታል፡፡

### 9. Salary Scale

1. The office shall study salary scales for the use of prison police officers, present same through the bureau to the Council of the Regional Government as well as cause the execution of payments up on approval.
2. The salary scale shall contain the minimum and maximum levels applicable to each rank as well as indicate the salary increments to be given from time to time.

### 10. ስለ ደመወዝ መሻሻልና የእርከን ጭማሪ

1. የክልሉ ማረሚያ ቤት ፖሊሶች የደመወዝ ጣሪያ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በየጊዜው እየታየ እንደሁኔታው ተሻሽሎ የሚወሰንና የሚፈፀም ይሆናል፡፡
2. ከፍተኛ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የሥራ አፈፃፀም ውጤት ላገኙ የማረሚያ ቤት ፖሊሶች እንደየስራ አፈፃፀማቸው ውጤት መጠኑ የተለያየ የደመወዝ ደረጃ ሊወሰንላቸው ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ስር የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለሁለት ተከታታይ አመታት የሥራ አፈፃፀም ውጤቱ አጥጋቢ የሆነ ማንኛውም ማረሚያ ቤት ፖሊስ በያዘው የማምረግ ደረጃ የእርከን ጭማሪ ያገኛል፡፡

### 10. Salary Reform and Scale Increment

1. The salary ceiling of prison police officers of the regional state shall, from time to time be conditionally reformed, as to be determined and executed by the Council of the Regional Government.
2. The salary increment to be made to those prison police officers with outstanding performances or above may be reformed and determined with different variations depending on the degree of their performance.
3. Without prejudice to the provisions of sub arts. (1) and (2) Of this article hereof, a prison police officer whose performance is found to be satisfactory for two consecutive years shall be entitled to obtain a scale increment in respect to the level of rank he has held.

### 11. ስለደመወዝ አከፋፈል

### 11. Payment of Salary

www.abyssinialaw.com



1. የማረሚያ ቤት ፖሊስ ደመወዝ የሚከፈለው በየወሩ የመጨረሻ ቀን ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባል ለአመት እረፍት ፈቃድ ሲወጣ የወጣበት ወር ደመዙ በቅድሚያ ይከፈለዋል፡፡
3. በቂ በሆነ ምክንያትና የሚሰራበት ክፍል ሲያምንበት እየሰራበት ያለው የወር ደመወዝ በቅድሚያ ሊከፈለው ይችላል፡፡

## 12. የደመወዝ ክፍያን ስለመያዝና ስለመቁረጥ

1. የማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ደመወዝ፡-

   ሀ. በማረሚያ ቤት ፖሊሱ ስምምነት
   ለ. በፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም
   ሐ.በህግ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ሊያዝ ወይም ሊቆረጥ አይችልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥሮች “ለ” እና “ሐ” መሠረት ከማረሚያ ቤት ፖሊሱ ደመወዝ ላይ የሚቆረጠው ገንዘብ መጠን የደመወዙን 1/3ኛ መብለጥ የለበትም፡፡

## 13. ስለ ልዩ ልዩ አበሎች

1. በማንኛውም ደረጃ ላይ የሚገኝ የማረሚያ ቤት ፖሊስ የቀለብ፣ በስምሪት ወቅት የሚደረግን ወጭ የሚያካክስ የመጓጓዣ አበልና እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰን ሌላ አበል ይከፈለዋል፡፡
2. አንድ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከፍ ወዳለ የሥራ ደረጃ በጊዜያዊነት ወይም በውክልና ተመድቦ እንዲሠራ ሲደረግ የሀላፊነቱን ደረጃ ባገናዘበ ሁኔታ በወካዩና በተወካዩ ደመወዝ መካከል ያለውን ልዩነት ከሀያ አምስት እስከ ሀምሳ በመቶ

1. The salary of prison police officers shall be paid on the last day of every month.
2. Any prison police officer shall be entitled to advance payment of his monthly salary at the time of taking his annual leavl.
3. With Sufficient justification and full understanding of the department in which he is assigned, a prison police officer may be entitled to advance payment of his monthly salary.

## 12. Withholding and Deduction of Salary

1. The salary of any prison police officer may not be withheld or deducted except in accordance with:
   a. The consent of the prison police officer;
   b. A court order; or
   c. The provisions of the law.
2. The amount of monthly deductions from the salary of a prison police officer made pursuant to sub-art.(1), Letters “b” and “c” of this article hereof may not exceed one third of his salary.

## 13. various Allowances

1. A prison police officer found at any level shall be paid allowances for food, transport in compensation of the expense spent while in deployment and other allowances to be determined as may be necessary.
2. A prison police officer shall, where he is assigned to a higher position of work temporarily or through agency, be entitled to a payment of 25 up to 50% of the difference between the salaries of the principal and agent, having regard to the degree of his responsibility. Details of the execution shall be

www.abyssinialaw.com



እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

determined by a directive.

## ክፍል አራት
## የህክምና አገልግሎትና ልዩ ልዩ ፈቃዶች

### 14. የህክምና አገልግሎቶች

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ሲታተም ወይም በሥራ ምክንያት ጉዳት ሲደርስበት በጽ/ቤቱና በየደረጃው ባሉ ማረሚያ ቤቶች የህክምና ክፍልና በማንኛውም የመንግስት የህክምና ተቋማት ተከፋፍሎለት የህክምና አገልግሎት ያገኛል፡፡
2. የማረሚያ ቤት ፖሊስ ሚስት ወይም ባል ወይም እድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ልጅ ሲታመሙ በጽ/ቤቱና በየደረጃው ባሉ ማረሚያ ቤቶች የህክምና ክፍል ወይም ወደ ማንኛውም የመንግስት የህክምና ተቋም ተልከው በማረሚያ ቤቱ ወጪ የህክምና አገልግሎት ያገኛሉ፡፡
3. በማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ በጡረታ ላይ የሚገኝ ወይም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ ከሆነ ጡረተኛው ራሱና የጡረተኛው ወይም የሟች ሚስት ወይም ባል ወይም እድሜአቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆቹ ሲታመሙ የህክምና ክፍል ባላቸው ማረሚያ ቤቶች ነፃ የህክምና አገልግሎት ያገኛሉ፡፡
4. ከማረሚያ ቤቶች በኩል ለሀገር ውስጥ ከፍተኛ ህክምና የሚላኩ አባላትን የመጓጓዣ ወጪ በሚቀርበው ማስረጃ መሠረት ጽ/ቤቱ ይሸፍናል፡፡

### 15. ስለ ዓመት ዕረፍት ፈቃድ

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ደመወዝ

## PART FOUR
## MEDICAL SERVICE AND VARIOUS LEAVES

### 14. Medical service

1. Any prison police officer shall, whenever he falls sick or suffers from an employment injury, obtain medical services from the medical sections of prisons at any level as well as from any governmental health-institutions, with the expense being covered thereto.
2. Where any prison police office’s wife or husband or a child below the age of 18 years falls sick, he/she may obtain medical services from the medical facilities of prisons at all levels or be referred to any governmental health institutions, at the expense of the prison concerned.
3. Where any prison police officer at a retiring age, himself falls sick , or, in case he has passed away, his/her wife or husband or children below the age of 18 years become ill, shall obtain free medical services from those prisons with health-facilities.
4. The office shall cover the transportation expense of prison police officers sent to referral health institutions for further examination in the country as per the receipts they will have produced thereto.

### 15. Annual Leave

1. Any prison police officer shall have the right to

www.abyssinialaw.com



የሚከፈልበት የዓመት እረፍት ፈቃድ የማግኘት መብት አለው፡፡

obtain annual leave with pay.

2. ለአንድ አመት ያገለገለ የማረሚያ ቤት ፖሊስ 20 የሥራ ቀናት የዓመት እረፍት ፈቃድ ያገኛል፡፡

2. A prison police officer shall be entitled to annual leave of 20 working days for the first year of his service.

3. ከአንድ ዓመት በላይ ያገለገለ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ዓመት አንድ የሥራ ቀን እየታከለበት የዓመት እረፍት ፈቃድ ያገኛል፡፡ ሆኖም የሚሰጠው የአንድ አመት እረፍት ፈቃድ ከ30 የሥራ ቀኖች መብለጥ የለበትም፡፡

3. A prison police officer having a service of more than one year shall be entitled to an additional leave of one working day for every additional year of service; provided, however, that the maximum duration of the said annual leave may not exceed 30 working days.

4. በሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ቀደም ሲል የተሰጠ አገልግሎት ለዚህ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ አፈፃፀም የሚታሰብ ይሆናል፡፡

4. Previous service rendered by the prison police officer in any other government office shall be considered for the application of sub-art. (1) Of this article hereof.

5. የዓመት እረፍት ፈቃድ በተቻለ መጠን የጽ/ቤቱን ጥቅምና የማረሚያ ቤት ፖሊሱን ፍላጐት ባገናዘበ እቅድ መሠረት መሰጠት አለበት፡፡

5. In as much as possible, annual leave shall have to be given in accordance with the plan taking in to account the interests of the office and the needs of the prison police officer.

## 16. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ አሰጣጥ

## 16. Granting of Annual Leave

1. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ዘመን የሚባለው የጽ/ቤቱ የበጀት ዓመት ነው፡፡

1. The period of the annual leave ne the fiscal year of the office.

2. ልዩ ሁኔታ ካላጋጠመ ወይም የማረሚያ ቤት ፖሊሱ ተከፋፍሎ እንዲሰጠው ጠይቆ የቅርብ አለቃው ካልፈቀደለት በስተቀር የዓመት እረፍት ፈቃድ በፈቃድ ዘመኑ ውስጥ ሣይከፋፈል በአንድ ጊዜ መሰጠት ይኖርበታል፡፡

2. Annual leave shall have to be granted during the fiscal year at one time without interruption unless there exists an exceptional circumstance or such is so requested by the prison police officer and permitted by his immediate superior.

3. ለሥራው ጊዜ ሲባል የማረሚያ ቤት ፖሊሱ አመታቱ እረፍት ፈቃድ ሣይወስድ ከቀረ ፈቃዱ ወደሚቀጥለው ዓመት ይተላለፋል፡፡

3. Where the prison police officer has not been granted annual leave due to compelling duties, the leave shall be postponed to the next fiscal year.

4. የሥራው ሁኔታ በማስገደዱ ምክንያት ጽ/ቤቱ የአንድን የማረሚያ ቤት ፖሊስ የአመት እረፍት

4. Where the office has been unable to grant a prison police officer his annual leave within the same fiscal

www.abyssinialaw.com



ፈቃድ በበጀት አመቱ ውስጥ ሊሰጠው ያልቻለ እንደሆነ የበላይ ኃላፊው ለ2 የበጀት አመታት ሊያስተላልፈው ይችላል፡፡ ሆኖም የማረሚያ ቤት ፖሊሱ ያልተጠናቀቀበት የአመት እረፍት ፈቃድ በ3ኛው በጀት አመት ውስጥ መስጠት ይኖርበታል፡፡

5. በዚህ ደንብ መሠረት ያልተወሰደ ወይም ያልተላለፈ የአመት ፈቃድ ቀሪ ይሆናል፡፡

## 17.በህመም ወይም ከሥራ በመጣ ጉዳት ምክንያት ስለሚሰጥ ፈቃድ

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባል በህመም ምክንያት ሥራ መሥራት ካልቻለ በሐሚም ማስረጃ የተደገፈ የህመም ፈቃድ ያገኛል፡፡
2. ለአንድ ዓመት ሣይቋረጥ ለሚደርስበት ህመም ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከሚመለከተው የህክምና ተቋም በሚያቀርበው ማስረጃ መሠረት ህመሙ ከጀመረው ጀምሮ ለመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት ሙሉ ደመወዝና ለቀጣይ ሶስት ወራት ግማሽ ደመወዝ ይከፈለዋል፣ እንዲሁም ለ2 ወራት ያለ ደመወዝ የህመምፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
3. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ በተለያየ ወይም በተከታታይ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የተሰጠው የህመም ፈቃድ ስምንት ወር የደረሰ እንደሆነ ወይም በአራት አመት ውስጥ የተሰጠው የህመም ፈቃድ አስራ ሁለት ወር የደረሰ እንደሆነ ሌላ የህመም ፈቃድ አይሰጠውም፡፡
4. አባሉ ድኖ ሥራውን መጀመር ካልቻለ ወይም የሐኪሞች ቦርድ ለሥራ ብቁ አይደለም ብሎ ከወሰነ ከሥራ ይሰናበታል፡፡ የዳረጐት ክፍያ ወይም ጡረታ የማግኘት መብት አግባብ ባለው ህግ መሠረት ይጠበቃል፡፡

year owing to compelling reasons pertaining to the duties, the senior official of the office may authorize the postponement of the annual leave for two fiscal years; provided, however, that any accumulated leave shall be granted to the prison police officer in the third fiscal year.

5. The annual leave, not taken or postponed pursuant to this regulation shall be cancelled.

## 17. Leave to be Granted due to Sickness or employment Injury

1. Any prison police officer shall be entitled to a sick-leave certified by medical evidence where he is unable to perform his duties because of illness.
2. Any prison police officer, whose illness continues for one year without interruption shall be entitled to a sick-leave with full pay for the first three months and with half pay for the next three months as well as two months without pay, on the basis of the certificate he produces from the pertinent medical institution.
3. Where the duration of sick leave granted to any prison police officer exceeds eight months in a year or twelve months in four years, he shall not be granted another sick –leave.
4. Unless the officer recovers from his illness and resumes work, or where the board of medical doctors decides that he is permanently disabled, he shall be relived from his official duties, and his rights to obtain gratuity or pension shall be protected by the relevant laws.

www.abyssinialaw.com



5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሥራ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት አባል ከጉዳቱ ድኖ ወደ ሥራው እስኪመለስ ወይም በጉዳቱ ምክንያት ለዘለቂታው መሥራት ያልቻለ መሆኑ በህክምና ማስረጃ እስኪረጋገጥ ድረስ የህመም ፈቃድከሙሉ ደመወዝ ጋር ይሰጠዋል፡፡ ሆኖም የሚሰጠው የህመም ፈቃድ በማናቸውም ሁኔታ ከአስራ ሁለት ወራት መብለጥ የለበትም፡፡
6. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ በህመም ምክንያት ከሥራ ቢቀር ከአቅሙ በላይ ካልሆነ በስተቀር በተቻለ ፍጥነት መታመሙን ለመ/ቤቱ ማሣወቅ አለበት፡፡ ሆኖም ለተከታታይ 3 ቀናት ወይም በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከ6 ቀን በላይ በህመም ምክንያት ከሥራ የቀረ እንደሆነ ለመታመሙ የህክምና ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
7. በ12 ወር ጊዜ ውስጥ ከጉዳቱ ድኖ ወደ ሥራው መመለስ ያለመቻሉ በህክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ የመብት አጠባበቁ በጡረታ ህግ መሠረት ይፈፀማል፡፡
8. አባሉ ህክምናውን በአግባቡ ባለመከታተሉ ወይም በሐኪሙ የተሰጠውን ትእዛዝ ባለማክበሩ ህክምናውን ያጓተተ እንደሆነ የሚሰጠው የህክምና ፈቃድ ይቋረጣል
9. ለዚህ ደንብ አላማ "በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት" የሚለው ሃረግ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ህግ ውስጥ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

## 18. የወሊድ ፈቃድ

5. Without prejudice to the provisions of sub-art (2) of this article hereof, an officer who has sustained an employment injury shall be entitled to an injury leave with full pay until he recovers and resumes work or until it is medically certified that he is permanently disabled due to his injury; provided, however, that the leave so granted may not exceed 12 months.
6. Where any prison police officer is absent from work due to sickness, he shall, as soon as possible, notify of the illness to his office, unless prevented from so doing by force major; provided, however, that he shall produce a medical certificate in case of absence from work for three consecutive days or for more than six days with in a fiscal year.
7. Where it is certified that the officer is unable to recover and resume work within 12 months, the protection of his rights shall be dealt with pursuant to the provisions of the pension Law.
8. Where the prison police officer delay his recovery by not following up the treatment properly or by his non-observance of the physician's recommendations, his entitlement to medical benefits and leave shall cease.
9. For the purpose of this regulation, the term "Employment Injury" shall have the meaning given to it under the Labor Law.

## 18. Maternity Leave

www.abyssinialaw.com



1. ነፍሰ ጡር የሆነች የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከእርግዝናዋ ጋር በተያያዘ ለሚደረጉ ምርመራዎችና ህክምናዎች ከደመወዝ ጋር ፈቃድ ይሰጣል፡፡ ሆኖም የማረሚያ ቤት ፖሊሷ ስለ ምርመራውና ህክምናው የሀኪም ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ነፍሰ ጡር የሆነች የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከመውለዷ በፊት ሐኪም እንድታርፍ ካዘዘ ደመወዝ የሚከፈልበት ፈቃድ ታገኛለች፡፡
3. ነፍሰ ጡር የሆነች የማረሚያ ቤት ፖሊስ እወልዳለሁ ብላ ከገመተችበት ጊዜ አንስቶ መውለጃዋ እስኪደርስ ድረስ የሰላሣ ተከታታይ ቀናት ፈቃድ እንዲሁም ስትወልድ ከወለደችበት ቀን ጀምሮ የስልሳ ተከታታይ ቀናት የወሊድ ፈቃድ ከደመወዝ ክፍያ ጋር ይሰጣታል፡፡
4. የወለደችው የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ሲያልቅ ያልወለደች እንደሆነ እስከምትወልድበት ቀን ድረስ ባሉት የሥራ ቀናት የምትቆይበት እረፍት ፈቃድ ወይም በበጀት አመቱ የእረፍት ፈቃዷን መውሰድ ትችላለች፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተወሰነውን የወሊድ ፈቃድ ከጨረሰች በኋላ ብትታመምና ተጨማሪ ፈቃድ የሚያስፈልጋት መሆኑ በሐኪም ከተረጋገጠ በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 በተደነገገው መሠረት የህመም ፈቃድ መውሰድ ትችላለች፡፡

1. A pregnant prison police officer shall be entitled to a paid leave for medical examinations in relation with her pregnancy; provided, however, that the officer shall produce a medical certificate, to that effect.
2. A pregnant prison police officer shall be entitled to a paid leave before delivery if recommended by a physician.
3. A pregnant prison police officer shall be entitled to 30 consecutive days of leave before delivery as of the day of her guess to give birth and 60 consecutive days of maternity leave after delivery with pay.
4. If she does not deliver on the presumed date during her per-natal leave, she shall take additional leave until delivery or from her annual leave within the fiscal year.
5. The officer may be entitled to sick – leave in accordance with the provisions of article (17) Of this regulation if she becomes ill and needs an additional leave evidence by a medical recommendation after completion of her maternity leave as provided under sub-art (3) Of this article hereof.

## 19. የሐዘን ፈቃድ

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ የትዳር ጓደኛው፣ ተወላጁ ወይም እስከ ሁለተኛ ደረጃ የሚቆጠር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመዱ ወይም አብሮት የሚኖር የቤተሰቡ አባል የሞተበት እንደሆነ ደመወዝ የሚከፈልበት የሶስት ተከታታይ ቀናት የሐዘን ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

## 19. Mourning Leave

1. Any prison police officer shall be entitled to a mourning leave with pay for three consecutive days in the event of the death of his spouse, descendant, or any other relative, by consanguinity or affinity, up to the second degree.

www.abyssinialaw.com



2. የማረሚያ ቤት ፖሊሱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተመለከተው ውጭ የቅርብ ዘመድ ወይም ወዳጅ የሞተበት እንደሆነ ደመወዝ የሚከፈልበት የአንድ ቀን የሐዘን ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡ ሆኖም የሚሰጠው ፈቃድ በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከስድስት ቀን መብለጥ የለበትም፡፡

## 20. ልዩ ፈቃድ

ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ በሚከተለው ሁኔታ ከደመወዝ ጋር ልዩ ፈቃድ የማግኘት መብት አለው፡፡

1. ጋብቻ ሲፈፀም 3 የሥራ ቀናት
2. ለሚከታተለው ትምህርት ፈተና ሲወስድ ፈተናውን ለሚወስድባቸው ቀናት በሙሉ፣
3. በማንኛውም ደረጃ በሚገኝ የዳኝነት ወይም የምርመራ አካል እንዲቀርብ ሲታዘዝ የተፈለገበትን ጉዳይ ለሚያከናውንባቸው ቀናት፣
4. በህዝብ ምርጫ ስልጣን የሚይዙ የመንግስት ኃላፊዎችን ለመምረጥ ሲሆን ምርጫው ለሚወስድበት ጊዜ፣
5. በጽ/ቤቱ እቅድ መሠረት በተገኘ የትምህርት ወይም የስልጠና ዕድል የሚሣተፍ ሲሆን የተፈቀደለት ይኸው ትምህርት ወይም ስልጠና ለሚወስድበት ጊዜ፡፡

## 21. ያለ ደመወዝ ስለሚሰጥ ልዩ ፈቃድ

ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ፈቃድ ለመውሰድ የሚያበቃ አሣማኝ ምክንያት ካቀረበ የጽ/ቤቱን ጥቅም የማይጐዳ ሆኖ ሲገኝና የቅርብ አለቃው ሲያምንበት በአምስት አመት ውስጥ ለአንድ ጊዜ ብቻ ለ30 ተከታታይ ቀናት ደመወዝ የማይከፈልበት ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

2. A prison police officer shall be entitled to a mourning leave with pay for one day in the event of the death of his close relative or friend other than those specified under sub-art. (1) Of this article; provided, however, that such a leave granted accordingly may not exceed six days within a fiscal year.

## 20. Special Leave

Any prison police officer shall be entitled to special leave with pay on the following conditions:

1. Three working days, while concluding marriage;
2. For all the days of the examination, while taking exams in pursuance of his education;
3. For all the days to accomplish the purpose for which he has been called upon, when he is summoned by a court of any level or an investigating body;
4. For the period which the voting process requires; where he has to participate in an election of Government officials;
5. For the time taken by education or training granted him, where he has to participate in such activities obtained in accordance with the plan of the office.

## 21. Special Leave Without Pay

Any prison police officer may be entitled to a leave without pay for 30 consecutive days once in a period of five years where he applies for same on convincing grounds; provided, however, that the interest of the office is not to be at jeopardy and his immediate superior believes in such an action.

www.abyssinialaw.com



## 22. ስለፈቃድ አጠያየቅና አሰጣጥ

1. የጽ/ቤቱ ሥራዎች ተከታታይነት ኖሯቸው ሣይጓደሉ እንዲቀጥሉ የሚያስችልና የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባላትን ፍላጐት ግምት ውስጥ የሚያስገባ የአመት ዕረፍት ፈቃድ አሰጣጥ ኘሮግራም መዘጋጀት አለበት፡
2. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ የዓመት እረፍት ፈቃድን በጽሁፍ መጠየቅ ይኖርበታል፡፡
3. የማረሚያ ቤት ፖሊሱ ከአመት እረፍት ፈቃድ ውጪ ያሉና በዚህ ደንብ የተካተቱ ሌሎች ፈቃዶችን ጥያቄ አመች ሆኖ ባገኘው መንገድ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

23. ያለፈቃድ ስለመቅረት

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ሣይፈቀድለት ከሥራው የቀረ እንደሆነ የቀረበት ደመወዝ ይቀነስበታል፣ ሆኖም አባሉ ለቀረበት ምክንያት በቂ ወይም አሣማኝ ማስረጃ አቅርቦ ሙሉ ደመወዙን ለማግኘት ይችላል፡፡
2. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከ21 ቀን በላይ ለክፍሉ ሣያሣውቅ ከሥራው የቀረ እንደሆነ እንደከጅ ይቆጠራል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያው ይወሰናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለ ደንብ ልብስ፣ ትጥቅ፣ አርማና መታወቂያ

## 24. ስለ ደንብ ልብስና ትጥቅ እደላ

ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ የሚያገኘው የደንብ ልብስና ትጥቅ ሁኔታ በቢሮው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 25. ስለ ዓርማ

1. ጽ/ቤቱ የራሱ የሆነ ዓርማ የሚኖረው ሲሆን የህግ

## 22. Application for and Issuance of Leave

1. There shall be prepared a program of granting annual leave enabling the office to continuously carry out its duties without interruption as well as taking in to consideration the interests of the prison police officers alike.
2. Any prison police officer shall have to request for his annual leave in writing.
3. The prison police officer may, in any way favorable to him, present his request for those leave other than annual leave specified under this regulation.

## 23. Absence Without permission

1. Where any prison police officer is absent from work without leave, his salary of absence shall be deducted; provided, however, that he may receive his full salary by producing adequate or presumed deserter. Details of the execution shall be determined by a directive.

Any prison police officer who may have been absent from work for more than 21 days without notifying of same to his department shall be presumed deserter. Details of the execution shall be determined by a directive.

## PART FIVE

## UNIFORM,FIREARMS, EMBLEM AND IDENTITY CARD

## 24. Distribution of uniform and firearms

The condition of uniform and firearms to be provided for any prison police officer shall be determined by a directive to be issued by the Bureau.

## 25. Emblem

1. The office shall have an emblem of its own which

www.abyssinialaw.com



ተገዥነትን፣ ዲሞክራሲን፣ ሠላምንና ሰብአዊነትን እንዲሁም ሙያንና አስተማሪነትን የሚያንፀባርቅ ይሆናል፡፡

2. የጽ/ቤቱ ዓርማ በማረሚያ ቤት ፖሊሱ መለዮ፣ በመታወቂያ ካርድ፣ በደንብ ልብስ ላይና እንደ አስፈላጊነቱ በጽ/ቤቱ አማካኝነት በሚወሰነው ቦታ ላይ ሊሆን ይችላል፡፡

3. የዓርማ ቀለማት ዓይነት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

4. ከጽ/ቤቱ ፈቃድ ውጭ ዓርማውን ለማናቸውም አገልግሎት መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

## 26. ስለመታወቂያ

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ማንነቱን የሚገልፅና በጽ/ቤቱ የሚዘጋጅ የመታወቂያ ካርድና መለያ ቁጥር ይኖረዋል፡፡

2. የማናቸውም ማረሚያ ቤት ፖሊስ መታወቂያ ወረቀት ከዚህ በታች የተመለከቱትን ማካተት ይኖርበታል፤-

ሀ. የክልሉ መንግስት አርማ

ለ. የጽ/ቤቱ አርማ

ሐ. የአባሉ ሙሉ ስም

መ. ማዕረግ

ሠ. የሥራ ኃላፊነት

ረ. መለያ ቁጥር

ሰ. መደበኛ አድራሻ እና

ሸ. የደም አይነት

3. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባል መደበኛ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ሲጠየቅ የመታወቂያ ካርዱን ማሣየት አለበት፡፡

reflects obedience to law, democracy, peace and humanity as well as professionalism and exemplariness.

2. The emblem of the office may be placed on prison police caps, identity card, uniform and any other place to be so determined, as may be necessary

3. The type of the color for the emblem shall be determined by a directive to be issued by the Bureau

4. It is prohibited to use the said emblem for any purpose without the permission of the office.

## 26. Identity

1. Any prison police officer shall have an identity card and identification number to be issued by the office.

2. The identity card of any prison police officer shall consist of the following particulars:

A. The emblem of the Regional State,

B. The emblem of the office

C. Full name of the officer,

D. Rank,

E. Position or responsibility,

F. Identification Number,

G. Domicile , and

H. Blood type.

3. Any prison police officer shall have the obligation to shaoe his identify card on demand while carring out his normal duties.

www.abyssinialaw.com



## ክፍል ስድስት

## ስለ ማዕረግ፣ የደረጃ ዕድገትና ሽልማት

### 27. ጠቅላላ

የጽ/ቤቱ የማዕረግ ተዋረድ፣ ስያሜና እርከን እንደሚከተለው ይሆናል፦

1. የዝቅተኛ ማዕረግ ስያሜና ዕርከን
   - ሀ. ኮንስታብል
   - ለ. ረዳት ሣጅን
   - ሐ. ምክትል ሣጅን
   - መ. ሣጅን
   - ሠ. ዋና ሣጅን
2. የመካከለኛ ማዕረግ ስያሜና ዕርከን
   - ሀ. ረዳት ኢንስፔክተር
   - ለ. ምክትል ኢንስፔክተር
   - ሐ. ኢንስፔክተር
3. የከፍተኛ ማዕረግ ስያሜና ዕርከን
   - ሀ. ዋና ኢንስፔክተር
   - ለ. ምክትል ኮማንደር
   - ሐ. ኮማንደር

### 28. የማዕረግ ቆይታ ጊዜ

አንድ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ተከታዩን ከፍተኛ ማዕረግ ከማግኘቱ በፊት በያዘው ማዕረግ ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ለእያንዳንዱ ማዕረግ የተወሰነውን ጊዜ መጨረስ አለበት፡፡

## PART SIX

## RANL, PROMOTION AND AWARDS

### 27. General

The hierarchy, designation and steps of the rank employed by the office shall be as follows:

1. Designation and steps of the lower rank:
   - A. Constable
   - B. Assistant Sergent
   - C. Deputy Sergeant
   - D. Sergeant
   - E. Chief Seargent
2. Designation and steps of the medium rank:
   - A. Assistant Inspector
   - B. Deputy Inspector
   - C. Inspector
3. Designation and steps of the higher rank:
   - A. Chief inspector
   - B. Deputy Commander
   - C. Commander

### 28. Period of Stay In Rank

Aprison police officer shall finish the period of stay assigned to each rank as indicted on the table below before he is promoted to the next higher rank.

www.abyssinialaw.com



| ማዕረግ | በያዘው ማዕረግ የሚቆይበት ጊዜ | ለተፋጠነ እድገት የሚያስፈልገው ጊዜ | በተከታታይ የሚያገኘው የማዕረግ እድገት |
|---|---|---|---|
| ኮንስታብል | 4 | 3 | ረ/ሣጅን |
| ረ/ሣጅን | 3 | 2 | ም/ሣጅን |
| ም/ሣጅን | 3 | 2 | ሣጅን |
| ሣጅን | 3 | 2 | ዋና ሣጅን |
| ዋና ሣጅን | 3 | 2 | ረ/ኢንስፔክተር |
| ረ/ኢንስፔክተር | 3 | 1 | ም/ኢንስፔክተር |
| ም/ኢንስፔክተር | 3 | 2 | ኢንስፔክተር |
| ኢንስፔክተር | 3 | 2 | ዋና ኢንስፔክተር |
| ዋና ኢንስፔክተር | 3 | 2 | ረ/ኮማንደር |
| ረ/ኮማንደር | 3 | 2 | ኮማንደር |

## 29. የማዕረግ ዕድገት

1. አንድ የማረሚያ ቤት ፖሊስ

ሀ. ሊሾም የሚችልበት ክፍት የሥራ መደብ ሲኖር፣

ለ. ለሚሾምበት ክፍት የሥራ መደብ የሚያስፈልገው የትምህርት ደረጃ የሥራ ልምድና የሥራ አፈፃፀም ከሌሎች ተወዳዳሪዎች የተሻለ ሆኖ ሲገኝ፣

ሐ. የተሰጠው ተፈላጊ ስልጠና ካጠናቀቀ ለማዕረግ እድገት ብቁ ይሆናል፡፡

2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 28 ለረዳት ኢንፔክተርነት ስለሚያበቃው የመቆሚያ ጊዜ የተደነገገው ቢኖርም የኢትዮጵያ ፖሊስ ኮሌጅ የሚያወጣቸውን መመዘኛዎች የሚያሟላና በዝቅተኛ የማእረግ እርከን ላይ የሚገኝ ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ የሚሰጠውን ስልጠና ካጠናቀቀ ለረዳት ኢንስ8ክተርነት መወዳደር ይችላል፡፡

3. ከፍ ያለ ተግባር የፈፀመና የላቀ የሥራ ችሎታ ያሣየ

| Rank | Period of stay in Rank | Period of stay in rank necessary for accelerated promotion | Next rank of promotion |
|---|---|---|---|
| Constable | 4 | 3 | Assistant Sergeant |
| Assistant Sergeant | 3 | 2 | Deputy Sergeant |
| Deputy Sergeant | 3 | 2 | Sergeant |
| Sergeant | 3 | 2 | Chief Sergeant |
| Chief Seargent | 3 | 2 | Assistant Inspector |
| Assistant Inspector | 3 | 1 | Deputy Inspector |
| Deputy Inspector | 3 | 2 | Inspector |
| Inspector | 3 | 2 | Chief Inspector |
| Chief Inspector | 3 | 2 | Assistant Commander |
| AssistantCommander | 3 | 2 | Commander |

## 29. Rank promotion

1. Aprison police officer shall be eligible for promotion in rank where:
   A. There exists a vacant position for his appointment;
   B. His educational qualification, work expriance and efficienty required for the vacant position of possible appointment is found to be better than that of oter competitors;
   C. He has completed the necessary training rendered to him.
2. Notwithstanding the period of stay required for an assistant inspector in accordance with Article (28) Of this regulation, any prison police officer with a step of the alower rank may be entitled to compete for the rank of assistant inspector provided that he has fulfilled the criteria as are issued by the Ethiopia police college.
3. Any prison police officer who has rendered a special

www.abyssinialaw.com



የማረሚያ ቤት ፖሊስ በዚህ ደንብ አንቀጽ 28 ስር ለተመለከተው የተፋጠነ እድገት ብቁ ሊሆን ይችላል፡፡

4. አንድ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ተጨማሪ ስልጠና ወስዶ እና ከማረሚያ ቤት ፖሊስ ስራ ጋር ግንኙነት ላላቸው መስኮች እውቅና ባላቸው የሙያና የቴክኒክ ማሰልጠኛዎች፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ተምሮ በዲፕሎማ ወይም በዲግሪ የተመረቀ እንደሆነ የትምህርት ማስረጃው ለማእረግ እድገቱ አወሣሰን ግምት ውስጥ ይገባል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## 30. የማዕረግ ምልክት

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከደንብ ልብሱ ጋር የሚደረግ የማረሚያ ቤት ፖሊስነቱንና የሥራ ደረጃውን ሊያሣይ የሚችል የማእረግ ምልክት ያደርጋል፡፡
2. የማዕረግ ምልክቱ አሰራርና የቀለም አይነት የማዕረግ እርከኖችን ለመለየት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## 31. ስለ ማእረግ እድገት አሰጣጥ

1. በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት ቅጣት የተወሰነበት ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ቅጣቱ በይርጋ ቀሪ ካልሆነለት በስተቀር ውሳኔው ከተላለፈበት ጊዜ አንስቶ በሚቀጥሉት ሶስት ተከታታይ አመታት ለማእረግ እድገት መወዳደር አይችልም፡፡
2. አንድ የማረሚያ ቤት ፖሊስ የማእረግ እድገት ከማግኘቱ በፊት ያገኝ የነበረው ደመወዝ እድገት ላገኘበት ደረጃ ከተወሰነው መነሻ ደመወዝ በላይ ወይም ቀዚሁ ጋር እኩል የሆነ እንደሆነ አዲሱን

contribution in his servce and demonstrated an outstanding performance capability may be eligible for an accelerated promotion provided for under Art. (28) Of this regulation hereof;

4. Where any prison police officer takes additional training other than his training in the prison police profession and graduated with a Diploma or Degree in those fileds related to prison police service from the recognized vocational and technical institutions, colleges and Universties, his educational evidence shall be considered in the decision on his rank promotions; particulars shall be determined by a directive.

## 30. Rank Insignia

1. Any prison police officer shall wear a rank insignia with his uniform indicating that he is a prison police officer with a certain step of rank.
2. The mode and the type of color preferred for the rank insignia shall enable one to identify the steps of the rank. Particulars of the execution shall be determined by a directive.

## 31. Granting of Rank Promotions

1. Any prison police officer, against whom a penalty has been imposed, as a result of rigorous disciplinary offence, may not be eligible to compete for a rank promotion during the following three consecutive years from the day of the decision having been passed, unless the penality has been waived dueto period of limitation.
2. Where the salary of a prison police officer before his promotion is more than or equal to the starting salary determined for the new grade obtained by promotion, he shall be entitled to a payment of salary which is a step higer than thee previous one.

www.abyssinialaw.com



ደመወዝ ከማግኘቱ በፊት ያገኝ ከነበረው ደመወዝ ቀጥሎ ያለውን እርከን ደመወዝ ያገኛል፡፡

3. ቢሮው የደረጃ እድገት የሚሰጥበትን ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

## 32. ስለ ሽልማት

ጽ/ቤቱ በስራው የላቀ አስተዋጽኦ ላበረከተ ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ሽሣት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## አገልግሎት ስለማቋረጥና ስለማራዘም

## 33. በገዛ ፈቃድ ከሥራ ስለመሰናበት

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባል በማናቸውም ጊዜ የአንድ ወር ቅድሚያ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ሊለቅ ይችላል፡፡
2. መልቀቂያ ጠያቂው አባል ለሥራው እጅግ አስፈላጊና በቀላሉ ለመተካት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ የጽ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የመልቀቂያ ጥያቄውን ከሶስት ወር ለማይበልጥ ጊዜ ሊያራዝመው ይችላል፡፡
3. መልቀቂያውን የጠየቀው አባል የግዴታ አገልግሎት ዘመኑን ሣያጠናቅቅ ጥያቄውን ያቀረበ ወይም ልዩ ስልጠና ወስዶ የሚያስፈልገውን አገልግሎት ያላጠናቀቀ እንደሆነ ለተሰጠው ስልጠና የወጣውን ማናቸውንም ወጪ ለጽ/ቤቱ መተካት ይኖርበታል፡፡

## 34. በህመም ወይም ከሥራ በመጣ ጉዳት ምክንያት ለአገልግሎት ብቁ ስላለመሆኑ

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከተው የህመም ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራ መመለስ ካልቻለ የህክምና ማስረጃ

3. The bureau shall issue adetailed directive on matters of promotion in rank.

## 32. Awards

The office may grant awards to any prison police officer who has renderd an outstanding countribution in respect of his service. Details of the execution shall be determined by a directive.

## PART SEVEN

## TERMINATION AND EXTENSION OF SERVICE

## 33. Resignation

1. Any prison police officer may, giving a one-month prior notice in writing resgin at any time.
2. Where the service of the prison police officer is indispensable and it is impossible to easily replace him, the senior official of the office may delay the release sought for a period not exceeding three month.
3. A prison police officer who has applied for a resignation prior to completing the period of his obligatory service or has received special training but not rendered the required services shall re-imburse to the office all corresponding expenses incurred due to the training provided thereto.

## 34. Inability to Render Service due to Sikness or Employment Injury

1. Where a prison police officer is unable to resume work within the period of sick-leave specified under art.(17), sub art . (2) Of this regulation hereof, he shall, without a

www.abyssinialaw.com



ማያስፈልግ በህመም ምክንያት ለሥራው ብቁ እንዳልሆነ ተቆጥሮ አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡

2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 5 ድንጋጌዎች መሠረት የተሰጠው የህመም ፈቃድ ጊዜ ካበቃ በኂላ ወደ ሥራ መመለስ ካልቻለ በሥራው ምክንያት ጉዳት የደረሰበት አባል ለዘለቄታው መስራት አለመቻሉ በህክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ ከሥራ እንዲሰናበት ይደረጋል፡፡

## 35.በችሎታ ማነስ ምክንያት ከሥራ ስለመሰናበት

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ያለውን ዕውቀትና ችሎታ ተጠቅሞ የተመደበበትን ስራ ለማከናወን የተቻለውን ጥረት እያደረገ የሥራ አፈፃፀም ውጤቱ በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ከአጥጋቢ ነጥብ በታች ከሆነ ከሥራ ማሰናበት ይቻላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም ቀደም ባሉት ተከታታይ አምስት አመታት ከፍተኛ የሥራ አፈጎፀም ውጤት ሲያገኝ የነበረ አባል የሥራ አፈፃፀም ውጤቱ በተከታታይ ለ3 ጊዜ ከአጥጋቢ ነጥብ በታች ካልሆነ በስተቀር ከሥራ አይሰናበትም፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 ድንጋጌ መሠረት አንድን የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከሥራ ማሰናበት የሚቻለው፡-

   ሀ. የሚያስፈልገውን ስልጠና በመስጠት ወይም፣

   ለ. ከያዘው የሥራ ደረጃ ጋር ተመሣሣይ በሆነና ሊሰራው ወደሚችለው ሌላ የሥራ መደብ በማዛወር፣

   ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ሲሆን ቢያንስ ለአንድ አመት ወይም በንዑስ አንቀጽ /2/

requirement of medical certificate be deemed unfit for service and discharged from his duty to that effect.

2. The service of any prison police officer, who is unable to resume work following the expiry of sick-leave in accordance with the provisions of art. (17), SUB-ARTS. (3) And (5) of this regulation hereof and who is medically declared to be permanently incapable of working shall be terminated.

## 35. Termination on Grounds of Inefficiency

1. The service of any prison police officer may be terminated where his performance evaluation result has been found to be unsatisfactory for two consecutive evalution periods despite the fact that he has exerted all his knowledge and ability to accomplishthe duty he is assigned to.

2. Notwithstanding the provision of sub-art. (1) of this article hereof, aprison police officer, whose performance evaluation result has been found to be outstanding for the previous five consective years, may not be dismissed on grounds of inefficiency unless his performance result becomes unsatisfactory for the following three consecutive evaluation periods.

3. The termination of service under sub-arts. (1) or (2) Of this article hereof, shall be effected:

   A. After giving his a training required for his position; or

   B. By transferring him to another suitable position of similar frade;

   C. By giving him a one month prior notice, where the prison police officer is no longer able to improve

www.abyssinialaw.com



ሲሆን ደግሞ ቢያንስ ለአንድ አመት ተኩል እንዲሠራ ከተደረገ በኋላ አባሉ የሥራ አፈፃፀም ውጤቱን ለማሻሻል ያልቻለ እንደሆነ የአንድ ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ነው፡፡

his performance result after having been at work at least for one year in the case of sub-art. (1) or one and half year in the case of sub-art. (2) Of this article hereof.

## 36. በዲስኘሊን ምክንያት ከሥራ ስለማሰናበት

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከሥራ እንዲሰናበት የተላለፈበት የዲስኘሊን ቅጣት ውሳኔ በይግባኝ ያልተሰረዘለት እንደሆነ አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡

2. የቅጣት ውሳኔው በይግባኝ የተሻሻለለት ወይም የተሰረዘለት እንደሆነ በክርክር ወቅት ሣይከፈለው የቀረው ደመወዝ ታስቦ ያለወለድ ይከፈለዋል፡፡

## 36. Termination on Disciplinary Crounds

1. The service of any prison police officer shall be terminated where the penalty resulting from a decision imposed on him on disciplinary grounds has not been quashed on appeal.

2. Where the penalty imposed on him has been mitigated or cancelled on an appeal, the prison police officer shall be entitled to the payment of his salary withheld during the period of appeal without interst.

## 37. በዕድሜ ምክንያት አገልግሎት ስለማቋረጥ

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ አገልግሎቱ ካልተራዘመ በስተቀር በህግ ከተወሰነው የመጦሪያ እድሜ ከደረሰበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ያለ ተጨማሪ ሥነ-ሥርዓት አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡

2. አባሉ ጡረታ ከመውጣቱ ከሶስት ወር በፊት ይህንኑ በጽሁፍ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

## 37. Retirement

1. Unless it is so extended, the service of any prison police officer shall be termmated without any additional formality as of the last day on which he has attained the retirement age as determined by law.

2. The officer shall be notified of his retirement in writing three months in advance to such an action.

## 38. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ በማናቸውም ምክንያት አገልግሎቱን ሲያቋርጥ ወይም ለማቋረጥ ሲጠይቅ ሲያከናውነው የነበረውን የሥራ አይነት፣ የአገልግሎት ዘመኑን፣ ሲከፈለው የነበረውን ደመወዝና ከሥራ የተሰናበተበትን ምክንያት የሚገልፅ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

## 38. Certificate of Service

Where the service of any prison police officer is terminated for any reason or where he so requests, he shall be provided with a certificate of service indicating the type of work he was engaged in, duration of his service, the amount of his current pay and the reason for termination thereof.

## 39. አገልግሎት ሲቋረጥ ስለሚፈፀም ክፍያ

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ አገልግሎቱን በሚያቋርጥበት ጊዜ የሠራበት ደመወዝና አበል

## 39. Severance Pay

1. Any prison police officer shall, whenever he terminates his service, be entitled to salary and allowances for the

www.abyssinialaw.com



ይከፈለዋል።

2. አግባብ ባለው የጡረታ ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የማረሚያ ቤት ፖሊስ በሞት ምክንያት አገልግሎቱ ሲቋረጥ ለህጋዊ የትዳር ጓደኛው ወይም በሥሩ ይተዳደሩ ለነበሩ ቤተሰቦቹ የሶስት ወር ደመወዙ ይከፈላቸዋል።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የማረሚያ ቤት ፖሊስ በሥራ ላይ እያለ የተሰዋ እንደሆነ የስድስት ወር ሙሉ ደመወዙ ከነቀለብ አበሉ ለትዳር ጓደኛው ወይም በፅሁፍ ላሣወቃቸው ቤተሰቦቹና ወራሾቹ ይከፈላቸዋል።

## 40. አገልግሎትን ስለማራዘም

1. አንድ የማረሚያ ቤት ፖሊስ የመጦሪያ እድሜው ከደረሰ በኋላ በአንድ ጊዜ እስከ አምስት አመት በጠቅላላው ከአስር አመት ለማይበልጥ ጊዜ አገልግሎቱን ማራዘም ይቻላል።

2. የአንድን አባል አገልግሎት ማራዘም የሚቻለው፡-

ሀ. የአባሉ ትምህርት፣ ልዩ እውቀትና ችሎታ ለጽ/ቤቱ ሥራ ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ፣

ለ. ለጊዜው የእርሱን ተተኪ አባል ማግኘት አለመቻሉ ሲረጋገጥ፣

ሐ. አባሉ ለሥራው ብቁ መሆኑ በህክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ፣ እና

መ. አባሉ አገልግሎቱን ለመቀጠል ሲስማማና የአገልግሎቱን መራዘም (ቢሮው) ሲፈቅድ ነው።

service he has already rendered.

1. Without prejudice to the relevant provisions of the pension laws, where the service of prison police officer is terminated due to death, an amount of sum equivalent to his three months' salary shall be paid to his legal spouse or incase he has no spouse, to his dependants whose names had officially been registered during his tenure.

2. Notwithstanding the provisions of sub-art. (2) Of this article hereof, where a prison police officer has been sacrificed while in active service, an amount of sum equivalent to his six months' salary shall be paid to his legal spouse, or case he has no spouse, to his dependants whose names had officially been filed during his tenure.

## 40. Extension of Service

1. The service duration of a prison police officer may be extended beyond his retirement age for a period up to five years at a time and for a period not exceeding ten years in total.

2. The duration of service of a prison police officer may be extended where:

A. His qualification, special skill and ability is found to be essential for the duties of the office;

B. It is not possible to replace him with anther officer for the time – being;

C. It is medically proven that he is fit for the service; and

D. He consents to the extension of the service and the Bureau authorizes such an extension.

www.abyssinialaw.com



## ክፍል ስምንት

## የማረሚያ ቤት ፖሊስ ሊኖረው ስለሚገባ ግዴታና ሥነ- ምግባር

### 41. ታማኝነትና ታዛዥነት

ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ፡-

1. መላ ጉልበቱንና ችሎታውን ለህገ-መንግስቱና ለሕዝብ ጥቅም በታማኝነት ማዋል አለበት፡፡
2. የሕዝብን እምነትና አክብሮት እንዲያገኝ በጽ/ቤቱም ሆነ ከጽ/ቤቱ ውጪ በማንኛውም ጊዜ መልካም ጠባይና ሥነ-ምግባር ሊኖረው ይገባል፡፡ እንዲሁም ለዚህ ደንብና ጽ/ቤቱ ለሚያወጣቸው ሌሎች የሥነ-ምግባር መመሪያዎች ተገዥ መሆን አለበት፡፡
3. በማንኛውም ጊዜ የሙያውን ክብር ለማስጠበቅ የሚያስፈልገውን ሁሉ አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡
4. የተመደበበትን መደበኛ እና ሌላውን ተመሣሣይ ሥራ ባለው ከፍተኛ እውቀትና ችሎታ መፈፀም አለበት፣
5. በሥራ ዝርዝሩ ላይ የተሰጡትን ተግባራትና ከበላይ ኃላፊው የሚተላለፉትን ትእዛዛት መፈፀም አለበት፡፡ በማናቸውም አኳኋን የበላይ ኃለፊው በሥሩ ለሚገኙት የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባሎች ለሚሰጠው ትዕዛዝ ህጋዊነት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 42. ስለ ሥራ ሰዓት

1. የማረሚያ ቤት አገልግሎት በቀን 24 ሰዓት በሣምንት 7 ቀናት በወር 30 ቀናትና በዓመት 365 (6) ቀናት ያለማቋረጥ ይሰጣል፡፡
2. የአንድ የማረሚያ ቤት ፖሊስ የሥራ ሰዓት በቀን 8 ሰዓትና በሣምንት 40 ሰዓት ሆኖ አገልግሎቱ የሚሰጠው በቀን ውስጥ ባሉት 24 ሰዓታት ወይም በሣምንት ውስጥ ባሉት ቀናት በመላ ይሆናል፡፡

## PART EIGHT

## OBLIGATIONS AND ETHICAL CONDACT OF PRISON POLICE OFFICERS

### 41. Loyalty and Obedience

Any prison police officer shall:

1. devote with loyalty all his energy and caoacity for cause of the constitution and public interest;
2. Have good character and ethics at any time inside and outside the office so as to win public confidence and respect as well as obey to this regulation and other ethical directives to be issued by the office;
3. Fulfill all the requirements necessary to maintain his professional honour and integrity at any time;
4. Perform normal duties and other similar activities to his best Knowledge and ability;
5. Carry out all the functions vested in him as per his job description as well as orders passed on to him by his superior; provided, however, that the superior shall be responsible for the orders he has given under all circumstances.

### 42. Working Hours

1. Prison service shall, uninterruptedly, be rendered for 24 hours a day, 7 days aweek, 30 days a month and 365 (6) days year.
2. The normal working hours of any prison police officer constitute 8 hours a day and 40 hours a week; provided, however, that it has to be rendered 24 hours of a day or all days of a week.

www.abyssinialaw.com



3. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከተመደበበት ሰዓት የዘገየ ከሆነ ወይም ቀደም ብሎ የወጣ ወይም የቀረ እንደሆነ ይህንኑ ለቅብር አለቃው ማሣወቅ አለበት፡፡

4. አመቺ ባልሆነ አካባቢ ለሚሰራ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ጽ/ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 43. ከመደበኛ የሥራ ሰዓት በላይ መስራት ስለማስፈለጉ

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ በጽ/ቤቱ ልዩ ሥራ ምክንያት ለተከታታይ የሥራ ሰዓታት እንዲሰራ በሚመለከተው ኃላፊ የታዘዘ እንደሆነ ተጨማሪ የሥራ ሰዓት ይሠራል፡፡ ለሰራበት ተጨማሪ ሰዓትም የማካካሻ እረፍት ይሰጠዋል፡፡

2. ለማረሚያ ቤት ፖሊስ ተጨማሪ የሥራ ሰዓት የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡

## 44. ስለ ሴት የማረሚያ ቤት ፖሊሶች የስራ ሁኔታ

ሴት የማረሚያ ቤት ፖሊሶች በጾታቸው ምክንያት በአካላቸውና በጤናቸው ላይ ጉዳይ በሚያመጡ ሥራዎች ላይ አይመደቡም፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## 45. ሌላ ሥራ መስራት ስለሚከለከልበት ሁኔታ

ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ለጽ/ቤቱ የሚሰጠውን አገልግሎት የሚያጓድል፣ የተመደበበትን ስራና ኃላፊነት ተቃራኒ የሆነ ወይም ከሙያው ስነ- ምግባር ጋር የማይጣጣም ማንኛውንም ሌላ ስራ መስራት የለበትም፡፡

3. Where any prison police officer is late from the time he is due, or departs early or, is absent from work, he shall notify same to his immediate superior.

4. The office shall, having due regard to the circumstances, avail the necessary support to a prison police officer working in an unfavorable environment.

## 43. Necessity to Work in Excess of Normal Working Hours

1. Any prison police officer shall, where instructed by the concerned official to keep on working because of the special duty of the office, for consecutive working hours without interruption, work overtime; provided, however, that he shall be given a compensatory leave thereto.

2. It is prohibited to effecte an overtime pay to a prison police officer for the sake of his overtime duties.

## 44. Working conditions of women prison police officers

Women prison police officers may, because of their sex, not be assigned to duties, which are likely to cause harm on their body and health Details shall be determined bya directive.

## 45. Condition of Prohibition from other Engagements

prison police officer may engage himself in any other employment activity detrimental to the service he renders to the office, contrary to the duties and responsibilities pertaining to his assignment or thereby incompatible with his professional ethics thereto.

www.abyssinialaw.com



## 46. ፖሊሱ ከታራሚው ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ በሚያከናውናቸው ሥራዎች ሁሉ ታራሚውን የማገልገል ግዴታ አለበት፡፡
2. የህግ ታራሚዎችን ሰብአዊ መብቶች መጠበቅና ኢ-ሰብአዊ የሆነ አያያዝ እንዳይፈፀም ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 47. ምስጢር ስለመጠበቅ

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ መረጃው በህዝብ ዘንድ የታወቀ ካልሆነ ወይም መደበኛ ሥራውን በህጋዊ መንገድ ለመፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው በስተቀር በሥራው አጋጣሚና ምክንያት ወይም በሌላ አኳኋን ያገኘውን መረጃ ለማናቸውም ሰው መግለጽ የለበትም፡፡
2. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ስልጣን ባለው ኃላፊ በአግባቡ ካልታዘዘ ወይም በሥራ ላይም ሆነ ከሥራው ውጭ ጉዳዩን እንዲያውቀው ለሚገባው ሰው ካልሆነ በቀር በአሰራር " ምስጢር" የሆኑትን መረጃዎች ለሌላ ለማናቸውም ሰው መግለጽ የለበትም፡፡

## 48. ገንዘብ ስለመበደርና ስጦታ ስለመቀበል

1. የማረሚያ ቤት ፖሊስ በሥራው ምክንያት ከሚያጋጥመው ማንኛውም ሰው ገንዘብ መበደር የለበትም፡፡
2. ማንኛውም የማረማያ ቤት ፖሊስ ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ ስለሰጠው ወይም ወደ ፊት ስለሚሰጠው አገልግሎት ከማናቸውም ሰው ስጦታ ወይም ዋጋ መጠየቅና መቀበል የለበትም፡፡

## 46. Relationship to the Prisoners

1. Any prison police officer shall, in all the activities he undertakes, have the duty to serv the prisoners.
2. He shall protect the human rights of prisoners and thereby prevent any act of inhumane treatment.

## 47. Secrecy

1. Any prison police officer may not disclose information that happens to come in to his hands by virtue of his duties and any other condition to any one unless it is already known to the public or found to be necessary to accomplish his regular duties in a legal way.
2. Any prison police officer may not disclose information which has been declared "confidential" through practice unless he has duly been instructed to do so by a competent head or to a person who otherwise deserves to know such matters in or out of work.

## 48. Taking loan and Receiving Gifts

1. No prison police officer may borrow mony from any person whom he communicates with by virtue of his duties.
2. No prison police officer may demand or accept any gift or value in return to services rendered or expected to be rendered by him.

www.abyssinialaw.com



## 49. በመንግስት ስራና በግል ጥቅሞች መካከል ስለሚፈጠር ግጭት

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከዘመዱ ወይም ከወዳጁ ጥቅም ጋር በተያያዘ ሁኔታ ከሥራ ኃላፊነቱ ጋር ግጭት የሚፈጠርበት ጉዳይ ሲያጋጥመው ወዲያውኑ ለቅርብ አለቃው በጽሁፍ ማሣወቅ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተጠቀሰው ሁኔታ ሲያጋጥምና ጉዳዩ የተገለፀለት ኃላፊ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የጥቅም ግጭቱን ለማስወገድ በሚችል መልክ ሌላ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ተተክቶ ስራውን እንዲያከናውን ሊያደርግ ይችላል፡፡
3. የማረሚያ ቤት ፖሊስ ስራውን ሲያከናውን ለማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት አድልዎ ማድረግ ወይም ወገንተኝነት ማሣየት የለበትም፡፡

## 49. Conflict Between Official Duties and Individual Interests

1. Any prison police officer shall immediately report in writing to his superior whenever he encounters a matter coming in to conflict with his responsibilities in connection with the interest of his relatives or friends.
2. Where such a case as stipulated under sub art.(1) of this article arises, the superior, to whom the same has been reported, may, in order to resolve the conflict of interests and carryout the task, assign anther prison police officer by way of replacement.
3. Any prison police officer, while carrying out his duties, may not favour any political party or show partiality thereof.

## 50. ስለ ንብረት አያያዝና አጠቃቀም

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ለሥራው ሲባል የተረከበውን ንብረት በአግባቡ መያዝና መጠበቅ አለበት፡፡
2. ለስራ የተረከበውን ንብረት ጠብቆ ያልያዘና ያለአግባብ የተጠቀመ እንደሆነ በኃለፊነት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 50. Handling and Use of Property

1. Any prison polic officer shall have the responsibility to properly handle and utilize properties coming in to his possession and destined for duties.
2. Wherever a prison police officer fails to care for and thereby misuses properties destined for work, he shall be liable for the damage thereto.

## 51 ገቢን ስለማሣወቅ

ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከደመወዙ ሌላ የሚያገኘው ገቢ ቢኖር ለጽ/ቤቱ ማሣወቅ አለበት፡፡

## 51. Declaration of Income

Any prison police officer shall declare to the office any form of income other than salary, if obtained in accordance with a directive to be issued by the Bureau.

## 52. የደንብ ልብስ የመልበስ ግዴታ

ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ በሥራ ላይ ሲሆን የደንብ ልብሱን አሟልቶ መልበስ ይኖርበታል፡፡

## 52. Obligation to Wear Uniform

Any prison police officer is duty bound to wear a complete uniform while discharging his official duties.

www.abyssinialaw.com



## 53. የግል ንጽህናን ስለመጠበቅ

ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ የግል ንጽህናውን በሚገባ መጠበቅና ስለ ግል ንጽህናው አጠባበቅ በጽ/ቤቱ የሚወጡ መመሪያዎችን ማክበር ይኖርበታል።

## 54. ሌሎች ግዴታዎች

ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ፡-

1. ጽ/ቤቱን ሳያስፈቅድ ማናቸውንም ዓይነት የእርዳታ መዋጮ መሰብሰብ አይችልም።
2. እንደ ማረሚያ ቤት ፖሊስ አባላቱ የሥራ ማቆም አድማና ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ የለበትም።
3. የደንብ ልብስ ሲለብስ ጌጣጌጥ ማድረግ የለበትም። ሆኖም በባለትዳሮች አንፃር የጋብቻ ቀለበት ማድረግን ይህ ደንብ አይከለክልም።
4. ማንኛውም ወንድ የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባል ፀጉሩን መሣድጉ መገኘት የለበትም።
5. በግል ስራ ላይ እያሉ መደበኛ ዩኒፎርምን ለብሶ መገኘት ክልክል ነው።
6. የደንብ ልብስና የጦር መሣሪያ ለማንኛውም ሰው ማዋስ፣ መሸጥ፣ መለወጥና ማስያዝ አይቻልም።
7. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባል ጽ/ቤቱ ያወጣቸውንና በየጊዜው የሚያወጣቸውን የውስጥ መመሪያዎች ማወቅና መፈፀም አለበት።

## 53. Personal Hygiene

Any prison police officer shall have the responsibility to properly take-care of his personal hygiene and observe the guidelines to be issued by the office with respect to matters pertaining thereto.

## 54. Other Obligations

Any prison police officer:

1. May not collect any contribution in the form of aid failing the permission of the office;
2. May not engage in a strike and peaceful demonstrations, being a prison police officer;
3. May not wear any sort of jewelery while wearing a uniform; provided, however, that this provision shall not be meant to prohibit married persons from wearing a wedding-ring to that effect…
4. Any male prison police officer may not be allowed to grow his hair long.
5. It is forbidden to appear wearing a regular uniform while engaging in private affairs.
6. It is impossible to lend, sale,exchange for and have pawned one's uniform and firearms to and with any other person;
7. Any prison police officer shall have the duty to familiarize him self with the internal guidelines issued and to be issued by the office and implement same accordingly.

www.abyssinialaw.com



## ክፍል ዘጠኝ
## ስለ ማረሚያ ቤት ፖሊስ የመረጃ አያያዝና የእቅድ ክንውን ግምገማ

### 55. የግል ማህደርን ስለማዘጋጀት

1. ጽ/ቤቱ በሥሩ ለሚተዳደረው ለእያንዳንዱ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ዋና መፃፃፊያ የግል ማህደር እንዲኖር ያደርጋል፡፡
2. ለዚሁ ዓላማ በሚደራጀው የግል ማህደር ውስጥ አግባብነት ያላቸው መረጃዎች ተያይዘው እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡

### 56. የግል መረጃን ስለመመርመር

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ በጽ/ቤቱ ውስጥ በሚገኘው የግል ማህደሩ የተቀመጡትን መረጃዎች ጠይቆ ለማየትና ኮፒ አድርጐ ለመውሰድ መብት አለው፡፡
2. የጽ/ቤቱ ኃላፊና የሚመለከታቸው ሠራተኞች ካልሆኑ በስተቀር በጽ/ቤቱ ውስጥና ከጽ/ቤቱ ውጭ የሚገኙ ሌሎች አግባብ ያላቸው ሰዎች ወይም መሥሪያ ቤቶች የአንድን የማረሚያ ቤት ፖሊስ የግል ማህደር መመርመር የሚችሉት ከጽ/ቤቱ ኃላፊ ሲፈቀድላቸው ብቻ ነው፡፡
3. የማረሚያ ቤት ፖሊሱን ሳያሳውቁ በግል ማህደሩ ውስጥ ማናቸውንም ሌላ ማስረጃ ወይም መረጃ ማስቀመጥ የተከለከለ ነው፡፡

### 57. መረጃና የስራ ልምድ ማረጋገጫ ስለመጠየቅ

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ በግል ማህደሩ ውስጥ የሚገኘው ማስረጃ ለሶስተኛ ወገን እንዲገለጽለት ከጠየቀ በጥያቄው መሠረት ደብዳቤ ይፃፍለታል፡፡

## PART NINE
## MAINTAINACE OF RECORDS AND PLANPERFORMANCE EVALUATION OF THE PRISON POLICE

### 55. Arrangement of Personal Files

1. The office shall cause a personal file to be kept with the view to serving as the main tool of writing with regard to each prison police officer under its administration.
2. All relevant pieces of information shall henceforth be attached and kept within such personal file so organized for the purpose.

### 56. Access to Personal File

1. Any prison police officer shall have access to all information contained in his personal file or have a copy thereof.
2. With the exception of the head of the office and the concerned administrative staff, other persons in and out of the office or government offices shall have acess to the personal file of a prison police officer only when they are so authorized by the head of the office thereof.
3. It is prohibited to put any document or piece of information concerning him in to the personal file of a prison police officer without his prior knowledge.

### 57. Request for Information and Certificate of Work Experience

1. Where a prison police officer so requests that any sort of evidence contained in his personal file be revealed to a third party, a letter shall be written for him as per his desire.

www.abyssinialaw.com



2. የማረሚያ ቤት ፖሊሱ በሥራ ላይ እያለ የሥራ ልምዱ ተገልጾ በፅሁፍ እንዲሰጠው ከጠየቀ ሊሰጠው ይችላል፡፡

## 58. ስታትስቲካዊ መረጃዎች

ጽ/ቤቱ የማረሚያ ቤት ፖሊሱን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ስታትስቲካዊ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማጠናከርና የመተንመን ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

## 59. የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ዓላማ

1. የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ዓላማ የማረሚያ ቤት ፖሊሶች፡-
   ሀ. ስራቸውን በሚጠበቀው መጠን፣ የጥራት ደረጃና ጊዜ እንዲያከናውኑ
   ለ. ጠንካራና ደካማ ጐኖቻቸውን እንዲያውቁና
   ሐ. ለወደፊቱ የሥራ አፈፃፀማቸው እንዲሻሻልና ለሥራ ያላቸውን ተነሣሽነት እንዲያጐለብቱ ማስቻል ይሆናል፡፡
2. የሥራ አፈፃፀም ግምገማ በግልጽና ሥራው የሚመለከታቸው ወገኖች በተገኙበት በጋራ ይከናወናል፡፡
3. የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይፈፀማል፡፡

## ስለ ኃይል አጠቃቀም

## 60. በጥበቃና በእጀባ ወቅት ስለሚደረግ የኃይል አጠቃቀም

1. በማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ የሚደረገው የኃይል አጠቃቀም በህግ የተደገፈና ሕጋዊ ስልጣንን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

2. A prison police officer who is on service shall be given a certificate of work experience in writing where he so requests for same.

## 58. Statistical Data

The office shall have the responsibility to collect, compile and analyze various statistical data regarding the prison police officer.

## 59. Objective of plan Performance Evaluation

1. The objective of performance evaluation shall be to enable prison police officers to:
   A. Effectively discharge their duties in accordance with the expected amount, quality standard and time;
   B. Identify their strong and weak sides and
   C. Improve their future performance and develop self-initiative.
2. Performance evaluation shall be undertaken in a transparent manner having the collective participation of all the stake holders concerned with the duty together.
3. Performance evaluation shall be carried out in accordance with the directive to be issued by the Bureau.

## USE OF FORCE

## 60. Use of force while Exercising Security and Escort Duties

1. Any use of force exercised by a prison police officer shall be backed by law and thereby have the basis of legal authority.

www.abyssinialaw.com



2. በጥበቃ ወቅት የኃይል አጠቃቀም በሥራ ላይ ሊውል የሚችለው ፡-
   ሀ. የህግ ታራሚው በሚጠብቀው አባልና በሌሎች ታራሚዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ለማድረስ ሲሞክር፣
   ለ. ታራሚው በግሉም ሆነ በአድማ ታግዞ ለማምለጥ ሲሞክር ወይም በማምለጥ ላይ እንዳለ ሲደረስበት፣
   ሐ. ታራሚውን ለማስጣል ወይም ለማስመለጥ በሚወሰድ እርምጃ ወይም ሙከራ፣
   መ. በተቋሙ ላይ ከውጭም ሆነ ከውስጥ የሚሰነዘርን ጥቃት ለመከላከል በሚያስፈልግበት ጊዜ ይሆናል፡፡
3. በእጀባ ወቅት የኃይል አጠቃቀም ተግባራዊ የሚሆነው ታራሚው ወደ ፍ/ቤት፣ የሕክምና ተቋማት ወይም ሌሎች ስፍራዎች ታጅቦ በሄደበት ጊዜ ለማምለጥ በሚሞክርበት ወይም ታራሚዎችን የማስመለጥ እንቅስቃሴ በሚፈፅምበት ወቅት ይሆናል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀም በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል አስራ አንድ
## ስለዲሲኘሊን

### 61. የሥነ- ሥርዓት ቅጣት ዓላማ

የሥነ-ሥርዓት ቅጣት መሠረታዊ ዓላማ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከጥፋቱ እንዲታረምና ወደ ፊት ሥራውን በአግባቡ ለማከናወን እነዲችል ለማስተማር ወይም የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ለማሰናበት ነው፡፡

### 62. ቀላል የዲሲኘሊን ጥፋቶች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በዚህ ደንብ መሠረት ቀላል የዲሲኘሊን ጥፋቶች ሆነው ተመድበዋል፡-

2. Use of force may, while exercising security duties, be applicable where:
   A. The prisoner tries to cause a series harm on his escorting guard and other fellow prisoners;
   B. The prisoner tries to escape or discovered while escaping, either on his own or together with others in conspiracy;
   C. An action is taken or so attempted to apprehend a escaping prisoner or to the contrary;
   D. It is necessary to prevent an offence possibly launched against the institution, be it form within or without.
3. Use of force during escort may be applied where a prisoner tries to escape or acts to assist otherprisoner to escape while being accompanied to court, medical institutions or other places. Detailed execution shall be determined by a directive.

## PART ELEVEN
## DISCIPLINE

### 61. Objective of Discipilary penalities

The basic objective of disciplinary penalities is to rehabilitate a prison police officer who commits disciplinary breaches by making him learn from his fault and enable him to perform his duties properly or to discharge him from service in case he becomes recalcitrant.

### 62. Simple Disciplinary offences

The following are, pursuant to this regulation, classified as simple disciplinary offences:

www.abyssinialaw.com



1. የተሟላ የደንብ ልብስ አለመልበስ፣
2. ያለበቂ ምክንያት ወይም ያለፈቃድ ከሥራ መቅረት፣
3. በሰው ላይ ንቀት ማሣየት፣
4. በሥራ ቦታ ላይ ተገኝቶ ወደ ሥራ አለመሰማራት፣
5. የሥራ ሪፖርት ማዘግየት፣
6. የሥነ-ሥርዓት ጉድለቶችን አይቶ ለሚመለከተው ክፍል አለማሣወቅ፣
7. ለሥራ የተሰጡትን የደንብ ልብስ፣ የጦር መሣሪያ ተሽከርካሪና የመሣሠሉትን ንብረቶች ጽዳት ማጓደልና ደህንነታቸውን አለመጠበቅ፣
8. የግል ንጽህናን አለመጠበቅ
9. በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሣሣይነት ያላቸውን ሌሎች ግድፈቶች መፈፀም፡፡

1. Not wearing a complete uniformation;
2. Absence from official duties without sufficient cause or permission;
3. Contempt of human persons;
4. Not being on duty, though present at work place;
5. Delaying activity reports;
6. Failure to notify disciplinary breaches on sight to the concerned divison;
7. Failure to maintain the cleanliness of and protect the well being of the uniform, firearms, vehicles and the like properties given to him for carring out his duties;
8. Failure to take-care of personal hygiene;
9. Committing other breaches similar to those specified under this article hereof.

## 63. ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በዚህ ደንብ መሠረት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ሆነው ተመድበዋል፡-

ሀ. ማናቸውም የጥበቃ ሆነ የልማትና የአገልግሎት ሥራ እንዳይከናወንና ውጤት እንዳይሰጥ ማወክ፣ ማሰናከል ወይም ከሌሎች ጋር ማበር፣

ለ. በሥራ ምክንያት የታወቀን ምስጢር ማባከንና የሥራ እንቅፋት ሆኖ መገኘት፣

ሐ. በሥልጣን መባለግ ወይም ባልተሰጠ ሥልጣን መጠቀም፣

መ. የመሥሪያ ቤቱን መልካም ዝና በሚያጐድፍ አኳኋን ከሥራ ውጭ የደንብ ልብስ ለብሶ ለህዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ ተግባር መፈፀምና በአስነዋሪ ሁኔታ ውስጥ መገኘት፣

ሠ. ስብሰባዎችን ረግጦ መውጣት፣

## 63. Rigorous Disciplinary Offences

The following are, pursuant to this regulation categorized as rigorous disciplinary offences:

A. To disturb, obstruct or so collaborate with others against any security, as well as development and service rendering duties so that such may not be carried out and bear fruit;

B. To breach secrecy having become known to by virtue of official duties and being found to constitute an obstacle for work,

C. Abuse of power or act in an absence of authority;

D. To commit an immoral act in such away that it spoils the hifh regard of the office wearing uniform out of work place and being found in a disgracing situation;

E. To walk out of meetings ;

www.abyssinialaw.com



ሬ. በሥነ-ሥርዓት ጥፋት ተከሶ ቃልእንዲሰጥ ሲታዘዝ እምቢተኛ ሆኖ መገኘት፣

ሰ. የተመደበበትን ጥበቃ ትቶ መሄድና ከግዳጅ መሸሸት፣

ሸ. በተመደቡበት የዘብ ስራ ላይ ሳሉ መተኛት ወይም ሳይታመሙ ታምሚያለሁ በማለት ሥራን መበደል፣

ቀ. ወንጀል ሲፈፀም እያዩ ህግ በሚፈቅደው መሠረት ሪፖርት አለማቅረብ ወይም እርምጃ አለመውሰድ፣

በ. በህገ-ወጥ የቁማር ጨዋታ ላይ መገኘት ወይም በልማዳዊ ስካር ወይም በአደንዛዥ እጽ ተመርዞ በሥራ ላይ በደል ማድረስ፣

ተ. አላግባብ ጥቅም ለማግኘትም ሆነ በጥንቃቄ ጉድለት ሰነዶችንና መዝግብትን መሰረዝ፣ መደለዝ፣ መቅደድ ወይም መሰወር ወይም ለሚፈፅመው ተግባር መደለያ፣ ጉቦ ወይም ወሮታመጠየቅ ወይም መቀበል፣

ቸ. በሃሰተኛ የትምህርት ማስረጃና የሥራ ልምድ ማረጋገጫ ተጠቅሞ መገኘት ወይም ለመጠቀም መሞከር፣

ኀ. በቢሮ ውስጥና በሥራ አካባቢ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ወይም መሰል ተግባራትን መፈፀም፣

ነ. በመንግስት መዝገብ ወይም ሰነድ ላይ ማስፈር የሚገባውን አውቆ አለማስፈር ወይም መፃፍ የማይገባውን ጽፎ መገኘት፣

ኘ. በጽ/ቤቱ ወይም በአባላቱ ላይ ከህዝብና ከህግ ታራሚዎች የሚቀርበውን ክስና አቤቱታ በወቅቱ ተቀብሎና መርምሮ መልስ አለመስጠት፡፡

F. Becoming disobedient to appear and respond accordingly where he is summoned to do so due to charges for disciplinary offences;

G. Abandon the security work entrusted upon him and thereby flee away from official duties,

H. Sleep while in security watch on assignment or harm the duty by pretending to be sick though it is not true of him in actual fact;

I. Failure to bring report as per the prescriptions of the law or in ability to take actions as he encounters crime being committed;

J. Causing harm on official duties by Engaging, becoming alcoholic or drug addict;

K. Cancelling, falsifying, destroying or hiding documents and files by demanding an un due advantages or due to a negligent act, or demanding or receiving inducements, bribe or return-awards for the task he is meant to accomplishe;

L. Using or trying to use forged educational evidence and working experience certificates;

M. Performing sexual intercourse or similar acts inside an office and other work-places;

N. Failure to record which ought to be put in to or write what should not deserv being placed in a government files or documents, with full Knowledge.

O. Failure to receive, investigate and render timely response to any accusations and petitions to be put forward by the public and prisoners against the office or officers therein;

www.abyssinialaw.com



ኣ. የህግ ታራሚ ማስመለጥ ወይም እንዲያመልጥ መርዳት፣

ከ. ለሕግ ታራሚዎች ደህንነት ተገቢውን እርዳታ አለማድረግ፣

ኸ. በታራሚው ክልል የተከለከሉ እቃዎችን ማስገባት ወይም እንዲገቡ ድጋፍ መስጠት፣

ወ. የሕግ ታራሚዎችን ሰብአዊ መብት መርገጥ፣

ዐ. ከታራሚዎች ጋር ህገወጥ ተግባራትን መፈፀም፣

ዘ. ከታራሚዎች ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ወይም መሰል ተግባራትን መፈፀም፣

ዠ. ታራሚው ወደ ማረሚያ ቤት ሲገባ የሚያስቀምጠውን ንብረት በጊዜው አለመመዝገብ፣ እንዲበላሽ ማድረግ፣ ለግል ጥቅሙ ማዋል መደበቅ ወይም ማጥፋት፣

የ. ለሥራ የተሰጠውን የደንብ ልብስ፣ ትጥቅና ሌሎች ንብረቶች በመያዣነት መስጠት፣ መሸጥ፣ ማበላሸት፣ ለግል ጥቅሙ ማዋል፣ መጣል፣ ሳያስረክቡ መቅረት ወይም ለሌላ ግለሰብ ጥቅም እንዲውል ማድረግ፣

ደ. በማረሚያ ቤት ፖሊስነቱ ሥልጣን ተጠቅሞ እንዲጠብቅ የተሰጠውን ንብረትና ገንዘብ አላግባብ መጠቀም፣ ማጥፋት፣ መደበቅ፣ መስረቅ ወይም ማሰረቅ፣

ጀ. የታራሚውን የጊዜ ቀጠሮ አለመከታተልና በወቅቱ ፍ/ቤት እንዲቀርብ አለማድረግ፣

P. Causing the escape of prisoners or assistance thereof;

Q. Failure to provide appropriate support to the well being of prisoners;

R. Brining in items prohibited not to enter the prisoner's area or support their entrance;

S. Grossly violating or disregarding the human rights of prisoners;

T. Conspairing along with the prisoners in an illegal manner;

U. Performing sexual intercourse or acts of similar nature with the prisoners;

V. Failure to record on time any property put in custody by a prisoner entering the prison, allowing it to be spoiled using for personal advantages concealing or eliminating same thereof;

W. Pawning selling, spoiling using for personal advantages, dropping, failure to restore or facilitate for the advantage of another person, uniforms, firearms and other properties given to him for work.

X. Improperly using his authority as aprison police officer, abusing, wasting,concealing, stealing, stealing or causing to be stolen property or money put under his charges;

Y. Not following up the prisoner's call for appearances and failure to bring him to court on prescribed times.

www.abyssinialaw.com



## ክፍል አስራ ሁለት

## የሥነ-ሥርዓት ቅጣት ዓይነቶችና አፈፃፀማቸው

### 64. የሥነ-ሥርዓት እርምጃ አወሣሰድ ደረጃዎች

1. በማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ላይ የዲሲኘሊን ቅጣት ከመወሰኑ በፊት ፈፀመ የተባለውን የዲሲኘሊን ጉድለት በጽሁፍ እንዲያውቀው ተደርጐ ራሱን የመከላከል እድል ይሰጠዋል፣
2. በከባድ የዲሲኘሊን ጥፋት ምክንያት የቅጣት ውሣኔ የሚሰጠው በጽ/ቤቱ ሲሆን ለዚሁ አላማ በተቋቋመ የዲሲኘሊን ኮሚቴ የውሣኔ ሃሣብ አቅራቢነት ይሆናል፡፡
3. በቀላል የዲሲኘሊን ጥፋት ምክንያት የቅጣት ውሣኔ የሚሰጠው ዲሲኘሊን ባጉደለው የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባል የቅርብ አለቃ ይሆናል፡፡

### 65. በሥነ-ሥርዓት ጥፋት ምክንያት ስለሚወሰኑ የቅጣት አይነቶች

1. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ በተከሰሰበት ቀላል የዲሲኘሊን ጉዳይ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እንደ ጥፋቱ ሁኔታ ከዚህ በታች የተመለከተው ቅጣት ሊወሰንበት ይችላል፡-

ሀ. የቃል ማስጠንቀቂያ

ለ. የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ

ሐ. ከወር ደመወዙ እስከ አስር በመቶ የሚደርስ የገንዘብ መቀጫ

2. ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ በተከሰሰበት ከባድ የዲሲኘሊን ጉዳይ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እንደጥፋቱ ሁኔታ ከዚህ በታች የተመለከተው ቅጣት ሊወሰንበት ይችላል፡-

## PART TWELVE

## TYPES OF DISCIPLINARY PENALTIES AND THEIR EXECUTION

### 64. Steps of Taking Disciplinary Measures

1. Before imposing a disciplinary penalty on any prison police officer, he shall be informed of the offence allegedly committed, in writing and hence be given an apportunity to defend himself.
2. Rigorous penalties arising from serious disciplinary offences shall be delivered by the office upon the recommendation to be submitted by the disciplinary committee established for the purpose.
3. The penalties arising from simple disciplinary offences shall be delivered by the immediate superior of the prison police officer charged for lack of discipline.

### 65. Types of Penalties Imposed due to Disciplinary offence

1. Depending on the gravity of the offence, any one of the following penalties may be imposed on any prison police officer where he is found to have been guilty of committing simple disciplinary offences he is accused of:
   A. Verbal Warning;
   B. Written warning;
   C. Fine reaching up to 10% of his monthly salary.
2. Depending on the gravity of the offences, any one of the following penalties may be imposed on any prison police officer where he is found to have been guilty of committing rigorous disciplinary offences he is accused of:

www.abyssinialaw.com



ሀ. ከወር ደመወዙ ከአስር በመቶ በላይ እስከ ሶስት ወር ደመወዝ የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት፣

ለ. ከሥራ፣ ከማዕረግ ደረጃና ከደመወዝ ዝቅ መደረግ፣

ሐ. ከሥራ መሰናበት፡፡

## 66. ስለ ይርጋ

1. ቀላል የዲሲኘሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ የምርመራውን ጊዜ ሣይጨምር የፈፀመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ሶስት ወር እርምጃ ካልተወሰደበት በዲሲኘሊን ተጠያቂ አይሆንም፡፡

2. ከባድ የዲሲኘሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ጥፋት መፈፀሙ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በጥፋቱ ካልተከሰሰ በዲሲኘሊን ተጠያቂ አይሆንም፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ መወሰድ የሚገባውን የዲሲኘሊን እርምጃ ሣይወስድ የቀረ ማንኛውም ኃላፊ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

4. በዚህ ደንብ መሠረት የተጣለ የዲሲኘሊን ቅጣት ያለው ተፈጻሚነት ከአንድ አመት ሊበልጥ አይችልም፡፡ ሆኖም ቢሮው የእያንዳንዱን የዲሲኘሊን ቅጣት የይርጋ ዘመን በመመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡

A. Fine reaching up to three months' salary starting from over and above 10% of his monthly wage;

B. Demotion from postion, level of rank and salary grade;

C. Dismissal from job.

## 66. Period of Limitation

1. No disciplimary measure shall be put in to effect against a prison police officer who has committed an offence entailing simple disciplinary penalties unless such measure is taken within three months, excluding the time required for investigation, from the time such breach of discipline has been known.

2. No disciplinary measure shall be put in to effect against a prison police officer committing an offence entailing rigorous disciplinary penalty unless he has been formally charged due to the offence within a year from the time the breach of discipline has been known.

3. The official who has failed to take the measures specified under sub-art. 1 or 2 of this article hereof shall be held liable, to that effect, in accordance with law.

4. The period for the enforcement of any disciplinary penality imposed pursuant to this regulation may not be lengthened for more than a year; provided, however, that the Bureau may determine by a directive the period of limitation applicable to each disciplinary penality.

www.abyssinialaw.com



## ክፍል አስራ ሶስት

## የወንጀል ክስ በማረሚያ ቤት ፖሊስ ላይ ስለሚያስከትላቸው ውጤቶች

### 67. ከሥራ ስለማገድ

1. አንድን የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከሥራ አግዶ ማቆየት የሚቻለው ጽ/ቤቱ ለሥራው አፈፃፀም ይጠቅማል ብሎ ካመነበት ከሁለት ወር ለማይበልጥ ጊዜ ይሆናል፡፡

2. ጽ/ቤቱ አንድን የማረሚያ ቤት ፖሊስ በወንጀል ወይም በከባድ የዲሲኘሊን ጥፋት በህግ የከሰሰ እንደሆነ ድርጊቱ ከሥራ የሚያስወጣ መሆኑ ሲገመት ከሥራው ታግዶ እንዲቆይ ማድረግ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

### 68. ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው ወንጀል ስለተከሰሰ የማረሚያ ቤት ፖሊስ

ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ የተከሰሰበትን ወንጀል የፈፀመው ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ ሲሆንና ቋሚ ሆኖ የሚመራበትን ህግ ወይም ደንብ ሆን ብሎ በመተላለፍ ህገ-ወጥ ድርጊት ለመፈፀም ሣይሆን የተጣለበትን ግዳጅና ኃላፊነት ለመወጣት ሲል በነገሩ ሁኔታዎች መነሾ ተገዶ መሆኑን የዲሲኘሊን ኮሚቴ ያረጋገጠ እንደሆነ ጉዳዩ በሥነ-ሥርዓት ግድፈት የሚያስከትለው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. ፍ/ቤቱ የዋስ መብት ፈቅዶለት የሚከራከር ከሆነ በሥራው ላይ ሆኖ ሙሉ ደመወዝ ይከፈለዋል፡፡

## PART THIRTEEN

## EFFCTS OF CRIMINAL PROSECUTION ON PRISON POLICE OFFICERS

### 67. Suspension from Duty

1. A prison police officer may be suspended from duty by withholding his salary for a period not exceeding two months, if such a course of action is belived to be necessary for the accomplishment of the task,, on the part of the office.

2. The office may be able to suspend a prison police officer who happens by law to be under criminal or disciplinary proceedings with rigorous offence where such an act is presumed to have him removed from duty. Details shall be determined by a directive.

### 68. Prison Police Officer Accused of Crime on Account of his Duties

Where any prison police officer has committed a criminal offence, for which he is charged,while carrying out his official duties and the disciplinary committee proves that he has been rather compelled to so act under the circumstances of the case, with the view to discharging the obligations and responsibilities entrusted upon him, and not to commit illicit acts by intentionally violating laws and regulations instrumental to his permanent guidance, without prejudice to such penalties as may be imposed on him in pursuance of disciplinary proceedings:

1. He shall be paid full salary while remaining on duty provided that the court concerned releases him on bail.

www.abyssinialaw.com



2. ፍ/ቤቱ የዋስ መብቱን ሣይጠብቅለት ቀርቶ ማረሚያ ቤት የገባ እንደሆነ፡-
   ሀ. ጉዳዩን በያዘው ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ከስራ ታግዶና ደመወዙ ተይዞ ይቆያል፣
   ለ. በተከሰሰበት ወንጀል ፍ/ቤቱ ጥፋተኛነቱን አረጋግጦ የቅጣት ውሣኔ ያሳለፈበት እንደሆነ እገዳው ከፀናበት ቀን ጀምሮ ከሥራ ይሰናበታል፡፡
   ሐ. ጉዳዩ በይግባኝ ፍ/ቤት ታይቶ በነፃ ከተለቀቀ ወደ ስራው እንዲመለስና ተይዞ የቆየው ደመወዙም ያለ ወለድ ታስቦ ይከፈለዋል፡፡

2. Where he is denied the right to bail and thereby remains in detention:
   A. He shall be suspended from duty and his salary withheld until such time that the court having entertained the case renders finale decision thereof;
   B. He shall be dismissed from his official duties starting from the day suspension has been effected on, where the court finds him guilty of the criminal offence brought against him and imposes a penalty therewith;
   C. He shall be made to resume his official duties and collect his salary withheld excluding interes provided that he is acquitted freely by an appellate court.

## 69. ከሥራው ጋር ግንኙነት በሌለው ወንጀል ስለተከሰሰ የማረሚያ ቤት ፖሊስ

አንድ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከተግባሩ ጋር ግንኙነት በሌለው ወንጀል ተከሶ ከሆነ በዲሲኘሊን ኮሚቴ የሚሰጠው ውሣኔ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. ፖሊሱ የተከሰሰበት ቀላል በሆነ ጥፋት ሆኖ ፍርድ ቤቱ በዋስ ከለቀቀው ወደ ሥራው ተመልሶ ሙሉ ደመወዙን እያገኘ ይከራከራል፣
2. ፖሊሱ የዋስ መብት ሣይከበርለት ቀርቶ ከታሰረ ወይም በነፃ ከተለቀቀ በእስር ወቅት የነበረበትና ያልሰራበት ደመወዝ አይከፈለውም፡፡

## 69. Prison Police Officer Accused of Criminal Offence, Not Relating to His Duties

Where a prison police officer is accused of a criminal offence, not relating to his official duties, he shall, without prejudice to any decision possibly rendered by a disciplinary committee:

1. Defend him self by returning to his official duties and receiving his full salary provided that the court releases him on bail due to simple offence;
2. Not be entitled to any payment of his salary for the duration he has been out of work if he happens to be denied the right to bail and remains in detention or gets acquitted freely.

## 70. በፍርድ ቤት የተቀጣን የማረሚያ ቤት ፖሊስ ወደ ሥራው ስለመመለስ

1. አንድ የማረሚያ ቤት ፖሉስ ከሥራው ጋር በተያያዘ ወንጀል ተከሶና ከሶስት ዓመት ያለበለጠ የእስራት ቅጣት ተፈርዶበት እስራቱን ፈጽሞ እንደመጣ እስከ

## 70. Allowing a Prison Police Officer Sentenced by Court to Resume His Official Duties

1. Where the sentence passed on a prison police officer who has been accused of a criminal offence relating to his duties is found to be less than three years of

www.abyssinialaw.com



አንድ ወር ቀርቦ ሲያመለክት ጤናው ተመርምሮ ወደ ሥራው ሊመለስ ይችላል፡፡

2. አንድ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከሥራ ተግባሩ ጋር ግንኙነት በሌለው ወንጀል ተከሶ ከሁለት አመት ላልበለጠ ጊዜ የእስራት ቅጣት ተወስኖበት ቅጣቱን ፈጽሞ እንደወጣ እስከ አንድ ወር ቀርቦ ወደ ሥራው ለመመለስ ቢያመለክት የዲሲኘሊን ኮሚቴው፡-

ሀ. የፖሊሱን ጠባይና ችሎታ፣

ለ. የተከሰሰበትን የወንጀል ዓይነት፣

ሐ. ከመቀጣቱ በፊት ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ለተደጋጋሚ ጊዜ በከባድ የሥነ-ሥርዓት ጥፋት ያለተቀጣ መሆኑን በማመዛዘን ወደ ሥራው ሊመለስ የሚችልበት የውሣኔ ሃሳብ ባለበት ማረሚያ ቤት በኩል ሲቀርብ ጽ/ቤቱ የመጨረሻ ውሣኔ እንዲሰጠው ያደርጋል፣ በውሣኔው ካልተስማማ ፖሊሱ ለቢሮው ይግባኝ የማለት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

3. የማረሚያ ቤት ፖሊሱ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በእስራት ያሣለፈው ጊዜ በአገልግሎት ዘመንነት አይያዝለትም፡፡

## 71. በፍርድ የተቀጣን የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከሥራ ስለማሰናበት

ማንኛውም የማረሚያ ቤት ፖሊስ ከሥራው ጋር በተያያዘ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ወንጀሎች መፈፀሙ ተረጋግጦ በፍርድ ቤት የተቀጣ እንደሆነ ከሥራው እንዲሰናበት ይደረጋል፡-

ሀ. እምነት ማጉደል

ለ. መደለያ ወይም ጉቦ መቀበል

imprisonment, he may be allowed to resume his official duties if he applies within one month following his release after his health has been examined.

2. Where a sentence passed on a prison police officer who has been accused of a criminal offence unrelated to his duties is found to be not more than two years of imprisonment and where he applies to resume his official duties, the disciplinary committee shall cause him obtain final decision of the office in case his possible return to work is proposed on the part of his prison, having due regard to:

A. His behavior and capacity;

B. Type of criminal offence brought against him;

C. The fact that he has not repeatedly been punished for rigorous disciplinary offences within the last two years before the date of having been penalized where the prison police officer does not afree with the decision of the office, he shall have the right to lodge an appeal to the bureau.

3. The time spent while serving in jail by the prison police officer who has been found guilty of a criminal offence may not be considered to form part of his service years.

## 71. Dismissal of Prison police officer Sentenced by Judgment

Any prison police officer shall be dismissed from job, where convicted and sentenced by court, for having committed the following criminal offences in connection with his official Duties:

A. Breach of trust;

B. Reception of inducement or bribe;

www.abyssinialaw.com



ሐ. ስርቆት ወይም ውምብድና

መ. ማጭበርበር ወይም ማታለል

ሠ. በአድማ መሣተፍ

ረ. አደንዛዥ እጾችን መጠቀም

ሰ. ቁማር መጫወት ወይም ማጫወት

ሸ. በጥቅም ተደልሎ ታራሚን መልቀቅ

## ክፍል አስራ አራት

## የሥነ- ሥርዓት ክስ አመሰራረት፣ ክሱን የማጣራትና የመወሰን ሥልጣን

### 72. የሥነ-ሥርዓት ክስ ስለመመስረት

ማናቸውም የዲሲኘሊን ጥፋት ተፈጽሞ ሲገኝ ክሱ የሚመሰረተው በማረሚያ ቤት ፖሊሱ የቅርብ አለቃ ይሆናል፡፡ ክሱ የሚመሰረትበት ቅጽ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

### 73. ስለ ይግባኝ መብት

1. የቀረበው ክስ ቀላል የዲሲኘሊን ጥፋትን የሚመለከት ሆኖ በከሣሹ የቅርብ ኃላፊ ከተወሰነ አንድ ደረጃ ከፍ ላለው ኃላፊ ይግባኝ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ኃላፊ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡
2. የቀረበው ክስ በከባድ የዲሲኘሊን ጥፋት ላይ የተመሰረተ ከሆነ በተሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ጉዳዩ በይግባኝ እንዲታይለት ለጽ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ ይችላል፡፡ ኃላፊው የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡
3. ጥፋቱ ከሥራ ደረጃና ደመወዝ ዝቅ የሚያስደርግ፣ ከሥራ የሚያሣድግ ወይም የሚያስወጣ ከሆነ

C. Theft or robbery;

D. Fraudulent act or deceit;

E. Participation in conspiracy;

F. Taking or using additive substances;

G. Engaging ingambling or causing same to happen;

H. Releasing prisoners for receiving undue benefits.

## PART FOURTEEN

## INSTITUTION OF DISCIPLINARY PROCEEDINGS, INVESTIGATION AND DECISION-MAKING POWERS

### 72. Institution of Disciplinary Proceedings

Where any disciplinary offence is committed, the institution of its proceedings shall be effected by the immediate superior of the prison police officer concerned. The format of such proceedings shall be determined by a directive.

### 73. Right of APPeal

1. An appeal by any dissatisfied prison police officer may be lodged against the decision of his immediate superior on simple disciplinary offences to the next higher superior. The decision which such a superior renders shall final.
2. A Prison police officer, who is dissatisfied with the decision passed on him due to rigorous disciplinary offence, shall have the right to appeal to the head of the office. The decision which the head renders shall be final.
3. Where the offence is capable of entailing demotion from position of work and salary grade, suspension or dismissal from duty such a case shall be decided

www.abyssinialaw.com



በዲሲፕሊን ኮሚቴው የውሣኔ ሃሳብ አቅራቢነት በጽ/ቤቱ ኃላፊ ይወሰናል፡፡

4. በየደረጃው የሚገኙ የማረሚያ ቤት ኃለፊዎችና በክልል አቀፍ ጽ/ቤት የተመደቡ አባሎች በከባድ የዲሲፕሊን ጉዳይ የተከሰሱ እንደሆነ በጽ/ቤቱ በኩል ታይቶ ውሣኔ የሚሰጥበት ሲሆን ጉዳዩ ይግባኝ ከተጠየቀበት በቢሮው በኩል ታይቶ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጥበታል፡፡

## ክፍል አሥራ አምስት

## ስለ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች

### 74. ስለ ዲሲኘሊን ኮሚቴ መቋቋም

በማረሚያ ቤት ፖሊሶች የሚፈፀሙ ከባድ የዲሲኘሊን ጥፋቶችን በመመርመር የሚያጣራና ለየደረጃው ኃላፊዎች የውሣኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የዲሲኘሊን ኮሚቴ በዚህ ደንብ ይቋቋማል፡፡

### 75. የዲሲኘሊን ኮሚቴ አሰያየም፣ የአባላት ተዋጽኦና የአገልግሎት ዘመን

ተጠሪነቱ ለጽ/ቤቱ ሆኖ ፡-

1. የዲሲኘሊን ኮሚቴው እንደ አግባቡ በጽ/ቤቱ የበላይ ኃለፊ ወይም የማረሚያ ቤት የተዋረድ ኃላፊዎች አማካኝነት አንድ ሰብሳቢና አንድ ፀሃፊ የሚሰየሙለት ሲሆን በማረሚያ ቤት ፖሊሶች የሚመረጡ ሌሎች ሶስት አባላት ይኖሩታል፡፡
2. ከሚመረጡት የኮሚቴ አባላት መካከል ቢያንስ አንዷ ሴት መሆን አለባት፡፡
3. የኮሚቴው አባላት በሥራ ልምዳቸው፣ በታታሪነታቸው፣በታማኝነታቸው፣ በፍትሃዊነታቸውና

upon by the head of the office depending on the recommendation of the disciplinary committee;

4. Where Prison heads at all levels and those members of the prison police assigned in the regionwide office are charged for having committed rigorous disciplinary offences, such a case shall be entertained, however, that, when an appeal is lodged, the final decision of same shall be rendered by the Bureau.

## PART FIFIEEN

## VARIOUS COMMITTEES

### 74.Establishment of the Discipline Committee

There shall be established a disciplinary committee, vested with the powers to investigate rigorous disciplinary offences committed by the prison police officer and thereby submit recommendation to the heads at all levels.

### 75. Designation of the Disciplinary Committee, Composition of Members and Term of office

Having been accountable to the office:

1. The disciplinary committee shall have a chair-person and a secretary to be designated by the head of the office or those heads of prisons of various hierarchies, as the case may be, as well as three other members to be elected by prison police officers.
2. At least one of committee members elected thereto shall be a woman.
3. Members of the committee shall, regarding their work experience, diligence, loyalty, fairness and ethical conduct, be of good repute and honored by their work-

www.abyssinialaw.com



በሥነ- ምግባራቸው መልካም ስም ያተረፉና በሥራ ባልደረቦቻቸው ዘንድ የተመሠከረላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

mates.

4. የኮሚቴው አባላት የአገልግሎት ዘመን ሁለት አመት ይሆናል፡፡ ሆኖም እንዳስፈላጊነቱ ለተከታዩ የአገልግሎት ዘመን እንደገና ሊሰየሙ ወይም ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

4. The term of office of the committee members shall be two years; provided, however, that they may be able to be designated or elected for the next trm, as deemed necessary.

## 76. የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር

ኮሚቴው በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ከባድ ጥፋቶች ተፈጽመው ሲገኙ ጉዳዩን መርምሮ የውሣኔ ሃሣብ ያቀርባል፣
2. ይህንን ደንብ ለማሻሻል የሚረዱ ሃሳቦችን ለጽ/ቤቱ ኃለፊ ያቀርባል፣
3. የዲሲኘሊን ጥፋቶችን በማጣራት ሂደት አስፈላጊ የመሰለውን የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባል ወይም ኃላፊ ጠርቶ መጠየቅ ይችላል፣
4. ይህንን ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ልዩ ልዩ ዝርዝር የአፈፃፀምና የአሰራር ሥነ -ሥርዓቶችን እያዘጋጀ ለጽ/ቤቱ ያቀርባል፡፡ ሲፈቀድምለትም በሥራ ላይ ያውላል፡፡

## 76. Powers and Duties of the Committee

The committee shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

1. To examine the matter and submit recommendations where rigorous offences are found to have been committed;
2. To provide opinions to the head of the office with the view to improving this regulation;
3. To call and quation any prison police officer or official thereof considerd appropriate in the process of investigating disciplinary offences;
4. To prepare a set of detailed execution and working procedures helpful for the implementation of this regulation and put in to effect upon approval.

## 77. ስለ ኮሚቴው የአሰራር ሥነ- ሥርዓት

የኮሚቴው የአሰራር ሥነ-ሥርአት እንደሚከተሉው ይሆናል፡-

1. በማናቸውም ስብሰባ ከአባላቱ መካከል 2/3ኛ የሚሆኑት ሲገኙ ምልአተ-ጉባዔ ይሆናል፣
2. ማናቸውም ጉዳይ በስብሰባው ላይ በተገኙበት አባሎች የድምጽ ብልጫ ይወሰናል፡፡
3. የኮሚቴው አባላት ድምፅ እኩል ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ስምምነት የኮማቴው ውሣኔ ሆኖ ያልፋል፣

## 77. Working Procedures of the committee

The working procedures of the committee ahall be as follws:

1. The presence of two thirds of the members of the committee at any meeting shall constitute a quorum.
2. Any matter shall be decided upon by a majority vote of members present at the meeting.
3. In case of a tie, the side, for which the chairperson has voted, shall be the final decision of the committee.

www.abyssinialaw.com



4. ኮሚቴው በድምጽ ብልጫ በሚወስንበት ጊዜ ሁሉ የአነስተኛው ድምፅ አስተያየት መመዝገብ አለበት::

## 78. ስለ ማዕረግና ደረጃ እድገት ኮሚቴ መቋቋም

የማረሚያ ቤት ፖሊስ የማእረግና የደረጃ እድገት ጥያቄዎችን መርምሮ ለጽ/ቤቱ የውሣኔ ሃሣብ የሚያቀርብ የማእረግና የደረጃ እድገት ኮሚቴ በዚህ ደንብ መሠረት በየደረጃው ይቋቋማል::

## 79. ስለ ኮሚቴው አሠያየም፣ የአባላት ተዋጽኦና የአገልግሎት ዘመን

1. የማዕረግና የደረጃ ዕድገት ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-
   ሀ. የጥበቃና የአባሎች አመራር ኃላፊ ….. ሰብሳቢ
   ለ. በማረሚያ ቤት ፖሊሶች ጠቅላላ ስብሰባ የማመረጡ ሁለት ተወካዮች ……..አባላት
   ሐ. የታራሚዎች አስተዳደር ኃላፊ ……….. አባል
   መ. ክፍት የሥራ መደቡ የሚገኝበት የሥራ ክፈል ኃለፊ ….. አባል
2. በማረሚያ ቤት ፖሊሶቹ ከሚመረጡት የኮሚቴው አባላት መካከል ቢያንስ አንዷ ሴት መሆን ይኖርባታል::
3. በኮሚቴው አባልነት ለማገልገል የሚመረጡት ሰዎች በሥነ- ምግባራቸው፣ በፍትሃዊነታቸውና በሥራ አፈፃፀም ብቃታቸው የተመሰገኑ ሆነው በጽ/ቤቱ ውስጥ ከ5 አመታት በላይ ያገለገሉ መሆን አለባቸው::
4. የኮሚቴው የአገልግሎት ዘመን ሁት አመት ይሆናል::

4. Whenever decisions of the committee are made by a majority vote, the opinions of the minority shall be recorded with their reasons of exception.

## 78. Establishment of Rank and Promotion Committee

There shall be established, at any level, as per this regulation, a rank and promotion committee, vested with the powers to submit proposals to the office by investigation matters of rank and promotion of prison police officers.

## 79. Designation of the committee, Composition of Members and Term of office

1. The rank and promotion committee shall have the follwing members:
   A. Head of Security and management of members………….. Chair person:
   B. Two representatives to be elected by the general meeting of prison police officers…….. members;
   C. Head of prisoners' Administration ……………………member;
   D. Head of the concerned section, in which the vacant position is created………………….member;
2. At least one of the members of the committee to be elected by the prison police officers shall be a woman.
3. The persons elected to serve as members of the committee shall be so honored for their good ethical conduct, fairness and performance effeiciency and have served for more than five years in the office.
4. The term of office of the committee members shall be two years; provided, however, that they be able to be

www.abyssinialaw.com



ሆኖም አባላቱ ከታመነባቸው ለአንድ ተጨማሪ የአገልግሎት ዘመን እንደገና ሊመጡ ይችላሉ፡፡

5. ኮሚቴው ከአባላቱ መካከል በምርጫ የሚሰየም አንድ ፀሀፊ ይኖረዋል፡፡

## 80. የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር

ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለጽ/ቤቱ ኃላፊ ሆኖ፡-

1. የተወዳዳሪዎች ምዝገባ በወጣው ማስታወቂያ መሠረት በትክክልና በተሟላ ሁኔታ መከናወኑን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣
2. የተወዳዳሪዎችን የትምህርት ማስረጃና የሥራ ልምድ መግለጫ ትክክለኝነት ይመረምራል፣ ያጣራል፣
3. ዝርዝር የነጥብ አሰጣጡ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ ለማእረግና ለደረጃ እድገት የቀረቡትን ተወዳዳሪዎች በመመዘኛው መሠረት እያወዳደረበደረጃ ያስቀምጣል፡፡
4. የተሻለ ነጥብ ያመጡትን ወይም ያመጣውን ተወዳዳሪ በመምረጥ ከውሣኔ ሃሣብ ጋር ለጽ/ቤቱ ኃላፊ ያቀርባል፣
5. ለማጣራት ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተገቢ የሥራ ክፍፍሎችን ሊያነጋግር ይችላል፡፡

## 81. ስለ ኮሚቴው የአሠራር ሥነ-ሥርዓት

ከዚህ በላይ የዲሲኘሊን ኮሚቴውን አስመልክቶ በአንቀጽ 77 ሥር የሰፈሩት ድንጋጌዎች ለማዕረግና ደረጃ እድገት ኮሚቴውም የአሠራር ስነ- ሥርዓቶች ሆነው በተመሳሳይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

elected for following term if they are so confided in.

5. The committee shall have a secretary to be designated from among its members through election

## 80. Powers and duties of the Committee

The committee, having been accountable to the head of the office, shall:

1. Follow and ensure that the registration of the competitors is carried out properly and perfectly in accordance with the notice issued;
2. Examine and verify the accuracy of the competitors' educational certificates and work experience documents;
3. With particulars of grading to be determined by a directive, cause a competition to be conducted between and among applicants for rank and promotion to the position available with the requirements and list them in orders of their respective results;
4. Select competing applicants or applicant with the highest result and submit same to the head of the office with its recommendations;
5. Be able to consult with appropriate sections where such an action is required for the purpose of investigatve activities.

## 81. Working Procedures of the Committee

The provisions regarding the disciplinary committee stipulated under art. (77) Hereinabove shall, mutatis-mutandis, apply to the rank and promotion committee, so as to serve the purpose of its working procedures, as well.

www.abyssinialaw.com



## ክፍል አስራ ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 82. ደንቡ ስለሚሻሻለበት ሁኔታ

ይህ ደንብ ጽ/ቤቱ የሚደርስበት የእድገት ደረጃ እየታየ እንዳስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል፡፡

### 83. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### 84. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ቢሮው ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚረዱትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 85. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ሕግ- ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ባህር ዳር**
**ጥቅምት 30 ቀን 1997 ዓ.ም**
**ዮሴፍ ረታ**
**የአማራ ብሔራዊ ክልል**
**ርዕሰ መስተዳደር**

## PART SIXTEEN

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 82. Conditions of Amendment of the Regulation

This regulation may be amended to the extent required by the level of development which shall have been attained by the office.

### 83. Inapplicable Laws

Any other Regulation Directive or Customary practice inconsistent with this regulation may not apply to matters provided for in this regulation.

### 84. Power to Issue Directives

The Bureau may issue detailed directives for the execution of this Regulation.

### 85. Effective Date

This regulation shall enter in to force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazette of the Regional State.

**Done at Bahir Dar**
**This 9th day of November, 2004**
**YOSEF RETA**
**Head of Government**
**of the Amhara National Regional State**